# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ

## ፩. ቅድመ ሢመት

### ሀ. ልደትና ትምህርት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፪ ዓ/ም በጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረ ኤልያስ በተባለው ታላቅ ደብር ከደጋግ ክርስቲያን ቤተሰብ ተወለዱ ። አባታቸው አቶ ወልደ ማርያም ውቤ እናታቸው እመት ዘርትሁን አደላሁ ይባላሉ ።

የቅዱስነታቸው አእምሮ ትምህርት ለመቀበል እንደደረሰ በተወለዱበት በደብረ ኤልያስ መሪጌታ ረዳኸኝና ግራ ጌታ ሣህሉ ከተባሉት መምህራን የንባብና የዜማን ትምህርት ተማሩ ። በዚሁ ደብር የቅኔና የመጽሐፍ ትርጓሜ ጉባኤ ዘርግተው ከሚያስተምሩት ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ገብረ ሥላሴ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ ። በመጻሕፍት ትርጓሜም የውዳሴ ማርያም ፣ የቅዳሴ ማርያም ፣ የወንጌል ትርጓሜ ፣ አጥንተዋል ። ቀጥሎም በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው ከመምህር (ሐዲስ) ተክሌ (በኋላ ንቡረእድ ተክለ ሃይማኖት) በመጨረሻም ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ይባሉ ከነበሩት ኢትዮጵያዊ ሊቅ የመጻሕፍተ ሐዲሳትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ጠንቅቀው ዐወቁ ። ማወቅ ብቻም ሳይሆን አስተምረው ብዙ ደቀ መዛሙርት ለቤተ ክርስቲያን አፍርተዋል ። መደበኛውን ትምህርታቸውን መናገር ነው እንጂ ያልሰሙአቸው የትርጓሜ መጻሕፍት አይገኙም ።

ከዚያም ለዚህ ከፍተኛ ክብር እንዲበቁ ቅዱስነታቸውን የእግዚአብሔር መንፈስ መርቷቸው መንፈሳዊውን ሕይወት በመምረጥ በ፲፱፻፴ ዓ/ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄደው በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ማዕርገ ምንኩስናን ተቀብለዋል ።

በዘመናዊው ትምህርትም ረገድ ግርማዊ ጃንሆይ በ፲፱፻፴፬ ዓ/ም የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሀገራቸውን ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የውጭ ቋንቋም ተምረው የዘመኑ ሥልጣኔ ተካፋዮች እንዲሆኑ ጽኑ ምኞታቸው ስለነበረ በግርማዊነታቸው ትእዛዝና በቅዱስነታቸው አቅራቢነት ሃያ ሊቃውንት ተመርጠው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚገኝ ክፍል በታወቁት በአቶ በትረ ጽድቅ ካሣ አስተማሪነት የውጭ ቋንቋ አጥንተዋል ። ይህም ት/ቤት በኋላ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ወደነበረበት ቦታ ተዛውሮአል ።

### ለ. ሐዋርያዊ አገልግሎት

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድና ትእዛዝ በመካነ ሥላሴ ገዳም (ዛሬ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ) መምህር ተብለው በአስተዳዳሪነት ተሾሙ ። ግርማዊ ጃንሆይ በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም አዲሱን የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መርቀው ታቦቱ በገባበትና የልዕልት ዘነበ ወርቅ ኃይለ ሥላሴና የልዕልት ጸሐይ ኃይለ ሥላሴ ዓፅም እንዲሁም በጠላት እጅ ተደብድበው የሞቱ አርበኞች ዐፅም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በዐረፈበት ጊዜ ቅዱስነታቸውን የበዓልና የዘውትር ሙያ ሽልማት ሸልመው የጥንቱም ያዲሱም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ሹመዋቸዋል ።

በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም የመካነ ሥላሴ ገዳም መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ተብሎ በግርማዊነታቸው ሲሰ



በመካነ ሥላሴ መምህር ሳሉ

የም አስተዳዳሪውም ሊቀ ሥልጣናት እንዲባል ስለተፈቀደ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከግርማዊ ጃንሆይ ከራስ ወርቅና ከላንቃ ካባ ጋር ሙሉ ሽልማት

ተሾልመው የመጀመሪያው የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ገዳም ሊቀ ሥልጣናት ሆኑ ።

ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነትና በንጉሠ ነገሥቱ ጥረት ኢትዮጵያውያን አበው ጵጵስና እንዲሾሙ በእስክንድርያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስምምነት ሲደረግ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የጳጳሳት ምርጫ ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከሯቱ ኢትዮጵያውያን ተመራጮች አንዱ ሆነው በከፍተኛ ድምፅ ስለተመረጡ ለሹመት ወደ ምድረ ግብጽ ሄዱ ። ይሁንና ሹመቱ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለሁለት ዓመታት ቢዘገይም ከሁለት ዓመታት በኋላ ጉዳዩ እልባት ስለአገኘ አምስቱ ተመራጮች ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፵ ዓ/ም እንደገና ወደ እስክንድርያ ሄደው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በነበሩት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ እጅ ከሌሎች አራት ኢትዮጵያውያን ጋር አቡነ ቴዎፍሎስ ጳጳስ ዘሐረርጌ ተብለው ተሾሙ ።

በ፲፱፻፵፪ ዓ/ም የካቲት ፲፭ ቀን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፈቃድ እንደራሴ ሆኑ ። በኢትዮጵያና በግብጽ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በነበረው ስምምነት መሠረት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በያዙት የሐረርጌ ጳጳስነትና እንደራሴነት ላይ በኢትዮጵያ የብፁዕ አቡነ ዮሳብ ወኪልነት ተሰጣቸው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከፍተኛውን የፓትርያርክነት መብት ካገኘች በኋላ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረርጌ ሊቀ ጳጳስ ተባሉ ። በዚህ ረገድ በመካነ ሥላሴ ገዳም መምህር ተብለው በአስተዳዳሪነት ፫ ዓመት በሊቀ ሥልጣናትነት ፱ ዓመት በጳጳስነት ፲፱ ዓመት በሊቀ ጳጳስነት ፲፭ ዓመት በድምሩ ሃያ ስምንት ዓመታት ለኢትዮጵያ መንፈሳዊ አገልግሎት አበርክተዋል ።

ከዚሁ ውስጥ ሃያው ዘመን በእንደራሴነት የሠሩበት ሲሆን በዚህ ረጅም የሆነ የመንፈሳዊ ሥልጣን ዘመናቸው እጅግ ከፍተኛና ፍሬያማ የሆነ የተቀደሰ አገልግሎት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከአበረከቱ በኋላ በተወለዱ በ፷፩ ዓመታቸው መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በተደረገው የሁለተኛው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ምርጫ አንደኛ በመውጣት ሁለተኛው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው ተመርጠዋል ። ይልቁንም የቅዱስነታቸውን ሁለተኛ ፓትርያርክነት ልዩ የሚ አደርገው በሀገር ውስጥ በመሾም የመጀመሪያው ቅዱስ አባት መሆናቸው ነው ።

## ሐ. ቅዱስነታቸው ከፈጸሙአቸው ታላላቅ ሥራዎች ጥቂቶቹ


ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ልዑል እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ አባትነት ስለመረጣቸው ሕይወታቸውን ለፈጣሪያቸው መሥዋዕት አድርገው ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ለክርስቶስ ፍቅርና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ዕድገት የፈጸሙአቸው ዐበይት ምግባራት ብዙዎች ሲሆኑ ለዝክረ ነገር ያህል ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን ።

ቅዱስነታቸው ሀብተ ትምህርት የተሰጣቸው መንፈሳዊ አባት እንደመሆናቸው እያሉ የቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ተስፋ ጥላበት የነበረው የመንፈሳዊ ኮሌጅ ከተቋቋመ በኋላ ቅዱስነታቸው ት/ቤቱን በመምራትና በማስተዳደር ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዘመናዊ ዕውቀት በር ከፋች የሆኑ ምሁራንን እንዲያፈራ አድርገዋል ። እያሉ መንፈሳዊ ወጣቶችንም ወደውጭ አገር ለመንፈሳዊ ትምህርት በመላክ ለቤተ ክርስቲያኗም ሆነ ለሀገር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ ምሁራንና ተመራማሪዎችን አስገኝተዋል ። ለዚህ ምስክሩ ማንም ሳይሆን ዛሬ በሕይወት ያሉት በተለያየ የማስተማርና ምርምር ፤ የመንግሥት ፤ የቤተ ክርስቲያን ወዘተ - - - ሥራ ላይ ያሉ ምሁራንና ጳጳሳት ናቸው ።

በሊቀ ሥልጣናትነታቸውም ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሥራዎች ሠርተዋል ። የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተሻሻለ እቅድ ሥራውን መምራት የጀመረው በቅዱስነታቸው ጥረትና ድካም ነበር ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያውያን አበው መርጣ ጳጳሳት ለመሾም እንድትችል ለረጅም ጊዜ በተደረገው ጥረት ውስጥ ቅዱስነታቸው ጉልህ ሚና ተጫውተዋል ። ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ በየጊዜው በተደረገው ጉዞ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን መልእክተኞች በመምራትና በውይይቱም ጉልህ ተሳትፎ በማድረግ ጥረቱ ፍሬአማ እንዲሆን ከአደረጉት መልእክተኞች መካከል የመጀመሪያውን ቦታ ይዘዋል ።

ቅዱስነታቸው በፈጸሙት ሐዋርያዊ ተልእኮ በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ሰዎች አስተምረው ለጥምቀተ ክርስትና አብቅተዋል ። ለምሳሌም ያህል በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም በባሌ ጠ/ግዛት ባደረጉት እድካሚ ጉዞ በገደብ እውራጃ ፤ በዶዶላ ፤ በሲሮፍታ ፤ በሄቤና በኮኮሳና በጋጣ እየተዘዋወሩ የወንጌልን ትምህርት በማስተማር ፳፬ ሺህ የእዋማና የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮችን በማሳመንና በማጥመቅ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ አድርገዋቸዋል ።



ቅዱስነታቸው በጽሕፈት ቤት ሥራ ላይ እንደነበሩ ፤

በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚካሄድ የሰብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ድርጅት መሥርተው በአዲስ አበባና በሌሎችም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች እንደ አባትነታቸው እየተዘዋወሩና በአድባራትና በገዳማትም እየተገኙ ምእመናንንና ቤተክርስቲያንን በይበልጥ ለማቀራረብ የምእመናኑም ቍጥር እንዲታወቅ ለማድረግ የሰብከተ ወንጌል ድርጅት አቋቁመዋል ። ከዚህም በቀር በመንበረ ፓትርያርኩ የወጣቶች ማእከላዊ ጽ/ቤት መሥርተው በየደብሩ ቅርንጫፍ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር እንዲቋቋምና ወጣቶች በመንፈሳዊ ተግባር በይበልጥ የሚጐለምሱበትንና ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚቀራረቡበትን መንገድ ከፍተዋል ። ቤተ ክርስቲያንም ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር ጎን ለጎን መራመድ ስለሚገባት ቅዱስነታቸው ዘመናውያን ሰባክያንን ቀሳውስትንና ዲያቆናትን በየጊዜው እያሠለጠኑ በመንፈሳዊ መስክ እንዲሰማሩ አድርገዋል ።

## መ. ቅዱስታነታቸው በሐረርጌ ሀገረ ስብከት የፈጸሙአቸው ሥራዎች

ቅዱስነታቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፈጸሙት የተቀደሰ ተግባር በዚህ ብቻ ሳይወሰን በሀ

ገር ውስጥ የዘመናውያን ቀሳውስትና ዲያቆናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች እንዲሠሩ በዘመን ብዛት ያረጁና የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ አድርገዋል ።

ቅዱስነታቸው የሐረርጌ ጳጳስ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በዚሁ ሀገረ ስብከት የሕዝቡን የትምህርትና የሃይማኖት ሕይወት የሚያሟሉ ታላላቅ ሥራዎች ሠርተዋል ። ከነዚህም ሥራዎች ዋና ዋናዎቹን ብንጠቅስ ፦—

አንደኛ በቅዱስነታቸው ስብከት ወደ ክርስትና ሃይማኖት የተመለሱት ፤ የምእመናን ቍጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛ በመሄዱ ምእመናን እግዚአብሔርን የሚያመልኩባቸው ፲፪ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት የግርማዊ ጃንሆይን ድጋፍ እየጠየቁና ምእመናኑንም እያተጉ በዘመናዊ መልክ እንዲሠሩ አድርገዋል ።

ሁለተኛ ቅዱስነታቸው በዚሁ ጠ/ግዛት ዋና ከተማ «ከማቴ ብርሃን» በሚል ስም የሚጠራ መንፈሳዊ ማኅበር አቋቁመው በልዩ ልዩ አቅጣጫ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርገዋል ። ማኅበሩም በየጊዜው ከአባሎቹ በሚያገኘው የገንዘብ ርዳታ አንድ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት ከፍቶ በዕውቀት በኩል የከተማው ሕዝብ እንዲጠቀምበት አድርጎአል ።

በቅዱስነታቸው አስታዋሽነት ከግርማዊ ጃንሆይ በተሰጠው ሰፊ አዳራሽ በየጊዜው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በልዩ ልዩ ምሁራን አማካይነት ለወጣቶች በጠቅላላው ለምእመናን እንዲሰጥ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው ።

ከዚህም ሌላ ማኅበሩ በቅዱስነታቸው ጥረት ከግርማዊ ጃንሆይም በተደረገለት ልገሳ ጭምር አንድ ዘመናዊ የሆነ ማተሚያ ቤት አቋቁሞ ከማተሚያ ቤቱ በሚገኘው ገንዘብ ትምህርት ቤት ከፍቶ እናት አባት የሞቱባቸውን ልጆች ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ በማስተማር ላይ ነው ።

ሦስተኛ ቅዱስነታቸው በሐረር ከተማና በቁልቢ ገዳም ሁለት ትምህርት ቤቶች አቋቁመው ብዙ ወጣቶች በሥጋዊና በመንፈሳዊ ትምህርት እንዲሠለጥኑ አድርገዋል ። በተለይ በቅዱስነታቸው በሐረር ከተማ የተቋቋመው የመምህራን ማሠልጠኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በየጊዜው እሠልጥኖ ያወጣቸው መንፈሳውያን ወጣቶች በጣም ብዙዎች ከመሆናቸውም በላይ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥተዋል ።

## ሠ. ቅዱስነታቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የፈጸሙአቸው ሥራዎች

ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም ጋር ለመቀራረብ በምታደርገው የተፋጠነ ርምጃ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በዘመናዊ መንፈሳዊ ሥልጣኔ ወደፊት መራመድ አስፈላጊ በመሆኑ ቅዱስነታቸው የኢት



የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ።

የጵያን ቤተ ክርስቲያን እየወከሉ በልዩ ልዩ ኢኩሚኒካል ጉባኤዎች ላይ በመገኘት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር አቀራርበዋታል ።

በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በእንግሊዝ አገር በርሚንግሐም ላይ በተካሄደው የሰንበት ት/ቤቶች ኢኩሜኒካል ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ተገኝተዋል ። በዚህም ጊዜ የሰንበት ኢኩሜኒካል ት/ቤት ጽ/ቤት ተቋቁሞአል ። የትምህርተ ክርስትና የሰንበት ት/ቤት ተብሎም ተሰይሞአል ።

በ፲፱፻፵ ዓ/ም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አምስተርዳም ላይ ሲቋቋም ቅዱስነታቸው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም በጉባኤው ላይ በመገኘት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል እንድትሆን አድርገዋል ።

በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ግሪክ አገር የገባበት ፲፱ ሺህኛ ዓመት ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት በተከበረ ጊዜ ቅዱስነታቸው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችላቸው ጥሪ መሠረት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም ከመገኘታቸውም ሌላ ማውንት አቶስ በተባለው ሥፍራ ላይ የሚገኙትን ከሃያ በላይ የሚሆኑትን ታሪካውያን ገዳማት በአፌሴል ጎብኝተው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የተላከውን ስጦታ አበርክተዋል ።

በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ደግሞ እንግሊዝ አገር ቺቼስተር በተባለው ከተማ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማእከላዊ ኰሚቴ ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል ።

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም ደንብ መሠረት በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ መልእክተኞች የሚገኙበት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ በየስድስት ወይም በየሰባት ዓመቱ አንድ ጊዜ እንዲካሄድ በተወሰነው መሠረት የመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ በ፲፱፻፵፮ ዓ/ም ኢቫንስተን (አሜሪካ) ላይ በተደረገ ጊዜ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን መልእክተኞች በመምራት በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል ።

እንደዚሁም በ፲፱፻፶፬ ዓ/ም ኒውዴልሂ (ሕንድ) ላይ በ፲፱፻፷ ዓ/ም ደግሞ ኡፕሳላ ስዊድን ላይ ጠቅላላ ጉባኤ በተደረገ ጊዜ ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያን መልእክተኞች በመምራት የጉባኤው ተካፋይ ሆነዋል ።

የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም የቅዱስነታቸውን መንፈሳዊ አባትነት አክብሮ በመመ



ዱስነታቸው በጉባኤው ላይ ንግግር ሲያደርጉ

ልክትና ችሎታቸውን በመረዳት ከፍ'ቱ የጠቅላላው ጉባኤ ፕሬዚዳንቶች አንዱ እንዲሆኑ ሁለት ጊዜ በማከታተል ስለመረጣቸው የደርግ መንግሥት በውንብድና ከሥልጣን አውርዶ እስከ አሠራቸው ጊዜ ድረስ ከሦስቱ ፕሬዚዳንቶች አንዱ ነበሩ ።

ከዚህም በቀር በ፲፱፻፶፮ ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ የተደረገው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በሀገራችን መዲና እንዲካሄድ የተዋጣለትም ዝግጅት እንዲደረግ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸውም በላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንም በመምራት በጉባኤው ላይ ተገኝተዋል ። ጉባኤውም የተሳካ ውጤት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል ።

ከዚህም በቀር በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም አቢጃን (አይቮሪኮስት) ላይ የተደረገውን የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ በፕሬዚዳንትነት መርተዋል ።

ከጥር ፪ ቀን እስከ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ በአፍሪካ አዳራሽ በተደረገው ጠቅላላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይም ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞችን በመምራት ተገኝተዋል ።

በ፲፱፻፷፰ እ - ኤ- አ- ናይሮቢ (ኬንያ/ላይ የተካሄደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ቴዎፍሎስን የሚቀጥለው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፕሬዚዳንት አድርጎ መርጦአቸው ነበር ። የደርግ መንግሥት ዕድሜአቸውን አሳጠረው እንጂ ።

ቅዱስነታቸው በእንደራሴነታቸው ወደ ውጪ ሀገር እየተላኩ በአሜሪካ በትሪኒዳድ በቶቤጎና በብሪቲሽ ጊያና በሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት በመላው ዓለም እንዲሠራጭ ሐዋርያዊ ጥረት አድርገዋል ።

## ለፓትርያርክነት ማዕርግ የቅዱስነታቸው መመረጥ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፪ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው የተመረጡት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከመጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ጀምሮ ዝግ ስብሰባ በማድረግ በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ላይ ተነጋግሮ ባወጣው የምርጫ ደንብና አፈጻጸም መሠረት ነው ። ደንቡ "ስለኢትዮጵያ ፓትርያርክ አመራረጥ የወጣ የ፲፱፻፷፩ ዓ/ም የምርጫ ደንብ" ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በዚህ ደንብ መሠረት መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በመንበረ ፓትርያርኩ በተፈጸመው የምርጫ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ለፓትርያርክነት ምርጫ እጩዎች ሆነው የቀረቡት ፫ ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ ፤ እነሱም ፩ኛ· በወቅቱ የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ እንደራሴና የሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ቅዱስነታቸው ፪ኛ· ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፫ኛ· ብጹዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ናቸው ። የእነዚህ አባቶች ስም ዝርዝር ከመጋቢት ፳፮ ቀን እስከ መጋቢት ፳፰ ቀን ድረስ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ ተቀምጦ ጸሎተ ቅዳሴ ሲደረግበት ከሰነበተ በኋላ መጋቢት ፳፱ ቀን በመንበረ ፓትርያርኩ በተደረገው ምርጫ ቅዱስነታቸው ከፍተኛውን ድምፅ ማለትም ከተሰጠው ድምፅ ፹ በመቶ አግኝተው ሊመረጡ ችለዋል። ይህም ምርጫ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ ለሕዝብ ይፋ ሆኗል ።

## የበዓለ ሢመቱ አከባበር

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ/ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ መኳንንቱና መሳፍንቱ ከልዩ ልዩ ሀገሮች የመጡ የሃይማኖት መሪዎች በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት ታሪካዊና ደማቅ በሆነ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ ውሏል ።

ኢትዮጵያ በ፩ ሺህ ፮፻ ዓመት የክርስትና ታሪኳ ውስጥ ከራሷ ተወላጅ ፓትርያርክ መርጣ በራሷ ምድርና በራሷ ሊቃነ ጳጳሳት ስትሾም የመጀመሪያ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን ለበዓለ ሢመቱ የተዘጋጀው ፕሮግራም የቤተ ክርስቲያንን ባህል ጠንቅቆ የያዘና እጅግ ሰፊ ነበር ።

ለበዓሉ አከባበር በወጣው ፕሮግራም መሠረት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከመንበረ ፓትርያርክ ተነሥተው የማዕርግ ልብስ በለበሱ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መብራት በያዙ ልኡካን "ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር" የሚለውን መዝሙር በሚያዜሙ መዘምራን ታጅበው ከጧቱ ፪ ሰዓት ከአሥር ደቂቃ ላይ ጸሎቱ ክርስቲ

ያኑ ዐውደ ምሕረት ሲደርሱ ከየአድባራቱ የተመረ ረጡ ቀሳውስትና ዲያቆናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር መግቢያ አንሥቶ እስከ ዐውደ ምሕረቱ ድረስ ግራና ቀኝ ተሰልፈው ተቀበሏቸው። በዚህም ወቅት የአ/አበባ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የደወል ድምፅ አሰሙ ።

ፓትርያርኩ ወደ ቅድስቱ ዘልቀው እንደቆሙ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሮ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በበዓሉ መካከል ለበዓለ ሢመቱ የተዘጋጀው ልዩ ጸሎት ቀጠለ ። በዚህም ጊዜ ከእኅትማማች ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ፓትርያርኮችና ሊቃነ ጳጳሳት በየተራ እየቀረቡ የጸሎቱ ተካፋዮች ሆነዋል ።

ቀጥሎም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተስማሚውን ጸሎት እያደረሱ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክ የማዕርግ ልብስ አልብሰው ፡ አክሊለ ክብሩን አቀዳጅተው አርዊ ብርቱን አስጨበጧቸው። ይህም በተደረገበት ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩት መዘምራንና ምእመናን «አክዮስ» ይደልዎ የሚለውን የማረጋገጫ ቃል ፫ ፡ ፫ ጊዜ በማሰማት ደስታቸውን ገለጹ ። ከዚህ በማያያዝም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ታላቁን የሰሎሞንን ኮርዶን ኒሻን አጠለቁላቸው ። ቅዱስነታቸውም ቃለ ሃይማኖት አሰሙ። በዚህም ወቅት ስለሢመተ ክብሩ ፲፯ ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ።

ከጸሎተ ወንጌል ቀጥሎ ያለው የጸሎተ ቅዳሴው ሥነ ሥርዓት የተካሄደው በአዲሱ ፓትርያርክ እየተመራ ሲሆን ጸሎተ ቅዳሴው ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ተከናውኖ ካበቃ በኋላ ፓትርያርኩ በዓምደ ወርቁ በር ላይ ቆመው በበዓሉ ሥነ ሥርዓት ላይ ተካፋይ የሆኑትን የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች የእጅ ሰላምታ በመስጠት አሰናበቱ ። ከዚያም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ታጅበው ወደ ዐውደ ምሕረቱ ሲወጡ መዘምራን በደመቀ ሽብሸባ ተቀበሏቸው ። ይህም እንዳበቃ የበዓሉ ተካፋይ የሆኑ የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች በየተራ እየተነሱ ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ሆኖ መመረጥና መሾም የተሰማቸውን ልባዊ ደስታ



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የፓትርያርኩን ልብስ ሲያለብሷቸው ።

www.ethiopianorthodox.org



አፄ ኃይለ ሥላሴ በበዓለ ሲመቱ ላይ ንግግር ሲያደርጉ

መግለጽ ንግግር አደረጉ ። ቀጥሎም ቅዱስነታቸ ውና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰፋ ያለ ንግግር ካደረጉ በኋላ ጠቅላላ ፕሮግራሙ ፯ ሰዓት ሲሆን ተፈጽሞ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ቤተ መንግሥታቸው ሲመለሱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሞተር ቢስክሌተ ኞች ታጅበው ወደ መንበረ ፓትርያርክ ሄዱ ።

ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ/ም የፓትርያርኩ በዓለ ሢመት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተከበረበት ጊዜ የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛት በብዙ ሺህ የሚገመት ሲሆን የቀረውም ሕዝብ የበዓሉ ሥነ ሥርዓትና አፈጻጸም ሁኔታ በቀጥታ በኢ ትዮጵያ ሬዲዮ ስለተላለፈለት ለመከታተል ችሏል። በዚህ ዕለት በጣም አስደናቂ ሆኖ የዋለው ከቀኑ ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ በቤተ ክርስ ቲያኑ አንጻር በሀሐይዙሪያ ተቀስቶ የነበረው ቀስተ ደመና ነው ።

# ከፓትርያርክነት በኋላ ያከናወኗቸው ዋና ዋና ሥራዎች ባጭሩ ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የረ ጅም ዘመን ነፃነት ያላት አገር መንፈሳዊ ድርጅት ብትሆንም ፣ እስከ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ድረስ ነፃነቷ የተሟላ አልነበረም ። ሙሉ ነፃነቷን ልትጐናጸፍየቻለችው የኢትዮጵያ መንግሥትና ራሷ ቤተ ክርስቲያኗ ለብዙ ዓመታት ያደረጉት ጥረት በእግዚአብሔር ፈቃድ ተሳክቶ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር በኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ካህናትና ምእመናን ጸሎተ ሢመት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሲሾሙ ነው ።

የቅዱስነታቸው በዓለ ሢመት የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ነፃነት የተረጋገጠ

በት እንደመሆኑ ፣ ከሀገር ውስጥ በወቅቱ ከነበሩት ንጉሠ ነገሥት ጀምሮ መሳፍንትና መኳንንት ካህናትና ምእመናን እጅግ በብዛት የተገኙበት ሲሆን የወዳጅነት ጥሪ የተደረገላቸው ከልዩ ልዩ ክፍላተ ዓለማት የመጡ ፓትርያርኮች ሊቃነ ጳጳሳትና የ፲፮ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችም ተገኝተው በዓሉን በታላቅ ክርስቲያናዊ ስሜት አክብረዋል ። የቅዱስነታቸውም ብልህ አመራር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዳዲስ የዕድገት ምዕራፎችን እንደሚከፍትላት መልካም ምኞታቸውን በጥልቅ ቃላት ገልጸዋል ። የቅዱስነታቸውን አስተዋይነትና ችሎታ አበክረው የተገነዘቡት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደተመኙት ሁሉ ቅዱስነታቸው ከበዓለ ሢመታቸው ማግሥት ጀምሮ ባደረጓቸው የስብከተ ወንጌል ፣ የልማትና የምግባረ ሠናይ እንቅስቃሴዎች በርካታ የዕድገት ምዕራፎችን ከፍተዋል ። ከእነዚህም መካከል በመጀመሪያ መጠቀስ የሚገባው የሰበካ ጉባኤ አደረጃጀት ነው ።

## ሀ· ሰበካ ጉባኤ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በ፬ኛው መቶ ዓመት ተመሥርታ በየዘመናቱ ለተነሡት የእምነቷና የትምህርቷ ተከታይ ነገሥታት ፣ ለመሳፍንቱ ፣ ለመኳንንቱ ለሠራዊቱና በአጠቃላይ ለምእመናን በየመልኩ መንፈሳዊ አገልግሎቷን ስታበረክት ፣ የምግባረ ሠናይ የትምህርትና የዕውቀት የባህልና የጥንታዊ ቅርስ መገኛ ሆና ኖራለች ። ነገር ግን ከአገልግሎቷ መስፋፋት ጋር አገልጋዮቿም እየበዙ በመሄዳቸውና ከአገልግሎታቸው ጋር ተመጣጣኝየሆነአበል ለመክፈል ባለመቻሏ ብቻ ሳይሆን ያለባትን የወደፊት ግዴታም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አርቀው በመመልከት የሰበካ አስተዳደር ጉባኤን መሥርተው በቃለ ዐዋዲ እንዲመራ አድርገዋል ።



በሰበካ ጉባኤ ለተሳተፉ ምእመናን ሽልማት ሲሰጡ


ዛሬ በዚህ በሰበካ ጉባኤ አማካይነት በሚገኝ ገቢ የእያንዳንዱ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት በየወሩ የማይናቅ ደመወዝ እየተከፈላቸው ኑሯቸውን ከማሻሻላቸውም ሌላ ሰበካው ከገቢው የተወሰነ ድርሻ ለወረዳ ፣ ወረዳው ለአውራጃው አውራጃው ለሀገረ ስብከቱ ፣ ሀገረ ስብከቱ ለመንበረ ፓትርያርክ የሚያስተላልፈው የገንዘብ ፈሰስ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሁለት እግሮቿ መቆም እንድትችል እያደረጋት ነው ። በዚህም ምክንያት ትናንት ይናቅና ይንኳሰስ የነበረው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መሆን ዛሬ የተከበረና የተወደደ ሆኗል ። ይህም የቅዱስነታቸው የድካም ውጤት ስለሆነ የታሪካቸው የማዕዘን ደንጋይ ሆኖ እንደሚኖር እሙን ነው ።

## ለ· የልማት ሥራ

ድኅረ ሢመተ ፕትርክና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱም ያስገኙት ሌላው ታላቅ የሥራ ፍሬ የልማት ድርጅት እንዲቋቋም ማድረጋቸው ነው ። ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ተልእኮ ብቻ ሳይሆን በተቻላት አቅም በልማት መስክም ከመንግሥት ጎን ሆና ረሀብን ፣ ድንቁርናን እና በሽታን የምትዋጋበትን መንገድ አስቀድመው ያልሙና ያስቡ ነበር ። በአንድ ወቅትም ለጋዜጠኞች በሰጡት ቃል "ወደፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ በሃይማኖት ሥራ ላይ ብቻ አይወሰንም በሀገሪቱ የልማት ሥራ ተካፋይ እንሆናለን ። የምእመናኑ ኑሮ የሚሻሻልበትን መንገድ መሻት ተገቢ ነው ። በኢኮኖሚ መጠንከር ያስፈልጋል ። ፍላጎታችንን አምላክ እንዲያሟላልን እንጸልያለን" ብለው ነበር ።

በዚህ ፍላጎት መሠረት ቅዱስነታቸው በሐምሌ ወር ፲፱፻፷ ዓ/ም በስዊድን ኡብሳላ ላይ ተሰብስቦ የነበረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን በልማት ተሳታፊ የምትሆንበትን ዘዴና ስልት ሲቀይስ በጉባኤው ላይ ተካፋይ ስለነበሩ በተከታታይ ዓመታት በተደረጉ ጥረቶች ሁኔታዎች ከተመቻቹ በኋላ በጥር ወር ፲፱፻፷፫ ዓ/ም "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በልማት ተካፋይነት" በሚል ርእስ የምክክር ጉባኤ በአዲስ አበባ ተደረገ። የዚህም ጉባኤ ውጤት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን ከታኅሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ራሱን ችሎ እንዲቋቋም አስቻለ ።

ይህ ኮሚሽን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በ፮ ሀገረ ስብከቶች ባቋቋማቸውየካህናት ማሠልጠኛዎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናትን በልዩ ልዩ ልማት ነክ ትም



የውሃ ልማት ሲጎበኙና መርቀው ሲከፍቱ

ሀርቶች እያወለጠን በመላ ሀገሪቱ ከማሠማራቱና የካህናቱንም ሕይወት ከመለወጡ ሌላ በድርቅ ለተ ጐዱ አካባቢ ሕዝቦች ፣ ድንገተኛ አደጋ ለደረሰባ ቸው ወገኖች በአጠቃላይ ርዳታ ለሚያስፈልጋ ቸው ኢትዮጵያውያን የገንዘብና የቍሳቍስ ርዳታ በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ በከፍተኛ ደረጃ እያሟላ በመምጣት ላይ ይገኛል ። ስለዚህ ይህን የመሰለ ክርስቲያናዊ ድርጅት እንዲ መሠረት ያደረጉት ቅዱስነታቸው ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ ናቸው ።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የልማት ሥራ ፍሬ ጐልቶ የሚታይበት ሌላው ድርጅት በንፋ መካኒ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አጠ ገብ ያቋቋሙት የእደ ጥበብ ድርጅት ነው ። "የማይ ሠራ አይብላ" በሚለው ሐዋርያዊ ትእዛዝ መሠረት ከጥንት ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲ ያን ካህናት በየአድባራቱና በየገዳማቱ ብራና በመዳ መጥ ፣ ቀለም በመበጥበጥ ፣ የቁም ጽሕፈት በመጻፍ ሥዕል በመሣልና መጽሐፍ በመደጎስ የእደ ጥበብ ሥራን ሲያካሄዱ መኖራቸው ዛሬ በዓይን የሚታዩት የብራና መጻሕፍትና ሥዕሎች ቋሚ ምስክሮች ናቸው በእንዲህ ያለ ጥንታዊ የሥነ ጥበብ ሥራ ላይ ዘመ ናዊ የእደ ጥበብ ሥራ ማለትም የእንጨት ፣ የሽመና የሥጋጃ ፣ የብረታ ብረት - - ወዘተ ሥራዎች ቢታከ ሉበት ለካህናቱ ሥራ መፍጠር ፣ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ም ጥቅም ማስገኘት መሆኑን ተገንዝበው ቅዱስ ነታቸው ከላይ የተጠቀሰውን የእደ ጥበብ ድርጅት በማቋቋማቸው ዛሬ ለበርካታ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሥራ እለኝታ ሆኖ ይገኛል ።

## ሐ· የምግባረ ሠናይ ድርጅት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዘመነ ፓትር ያርክነታቸው ከመሠረቷቸው ድርጅቶች መካከል የምግባረ ሠናይ ድርጅት አንዱ ነው ። እንደሚታወ ሰው በ፲፱፻፷፯ በወሎ ክ/ሀገር አስከፊ ድርቅ ተከ ሥቶ ብዙ ወገኖቻችን ለረሃብና ለሞት በተጋለጡ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች በጎ አድራጊዎች ጋር በመተባበር አቅሟ የፈቀደላትን የገ ንዘብ ርዳታ ብታደርግም ፣ በዚህ ብቻ መወሰን እንደማይገባት በመገንዘብ ቅዱስነታቸው አዲስ አበ ባ በሚገኘው በስዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ቅጽረ ግቢ አንድ የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅት እንዲ

ቋቋም አገዘው በረሀቡ ምክንያት እናትና አባታቸ ውን ያጡ ፶ ሊጋ ሕፃናት በዚህ ድርጅት እንዲረዱ አደረጉ ። ይህ በቅዱስነታቸው የተመሠረተው የሕ ፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ዛሬ ከ፴፮ የማያንሱ ሕፃ ናት ማሳደጊያ ተቋሞችን በመመሥረት ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በሚያገኘው ርዳታ ከ ፲፫ ያላነሱ ሕፃናትን በማሳደግና በመንከባከብ ላይ ይገኛል ። ይህም የፓትርያርክ ቴዎፍሎስ የአርቆ አስተዋይነት ሥራ ውጤት ነው ።

## መ. የውጭ ግንኙነትን ማጠናከር

ያለንበት ዘመን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግን ኙነታቸውን በተለያየ ድረጃ የሚ ያጠናክሩበትና ተባ ብረው የሚሠሩበት ዘመን ነው ። በዚህ መሠረት



ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የቆጵሮስ ፓትርያርክና ፕሬዚዳንት ኢትዮጵያን በጐበኙበት ወቅት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም ፓትርያርክ ከሆኑ ፯ ወር ባልሞላ ጊዜ ማለትም በጥቅምት ፲፱፻፷፬ ዓ/ም የግሪክ የቍስጥንጥንያና የእስክንድርያ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ባደረጉላቸው የወዳጅ ነት ጥሪ መሠረት እነዚህን ሀገሮች ለ፪ ሳምንታት ያህ ል በመጎብኘት ስለአርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መቀራረብና አንድነት ፣ ስለዓለም ሰላምና እውነተኛ ፍትሕ ስለሚሰፍንበት ሁኔታ በሰፊው በመነጋገር የቆየውን ግንኙነት እንደገና በማደስ እንዲጠና ከር አድርገዋል ።


በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም አጋማሽ ላይም በዩ . ኤ . ስ . አሜሪካ የሚገኙ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ባደረጉላቸው ጥሪ መሠረት በዚያ ታላቅ አገር ጉብኝት በማድረግ ለትምህርት ፣ ለልማት ሥራና ለቅርስ ጥበቃ የሚያግዙ በርካታ የገንዘብና የማቴ ሪያል ርዳታዎችን አስገኝተዋል ።

በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ደግሞ ከመንግሥት ጋር በመ መካከር የግብጽን ፓትርያርክ ሣልሳዊ ሲኖዳን ፣ የቈ ጵሮስን ሊቀ ጳጳሳትና ፕሬዝዳንት መቃርዮስን ፣ እና የመስኮብና የመላዋ ሩሲያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፒሜንን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንዲጐበኙ በመጋበዝ የቤተ ክርስ ቲያኒቱ የውጭ ግንኙነት እየተጠናከረ እንዲሄድ አድርገዋል ።

## ሠ. ሢመተ ጳጳሳት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት ከሊ ቃውንቷ መካከል መርጣ በራሷ ፓትርያርክ ቀብታ መሾም ከጀመረች አንሥቶ መንፈሳዊ የሥራ ዕድገት እያሳየችና በውጭ አገርም እየተስፋፋች በመምጣቷ አዳዲስ ጳጳሳትን መሾም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የካቲት ፬ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ፯ ቆሞሳት ለጵጵስና ማዕ ርግ ተመረጡ ። የእነዚህም ቆሞሳት የጵጵስና በዓለ ሢመት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እየተመራ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ/ም በቅድስት ሥላሴ ካቴ ድራል በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተፈጸሟል ። በዚህ ቀን ከተሾሙት ጳጳሳት መካከል ሁለቱ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ሆነው ሲመ ደቡ የቀሩት ፭ቱ በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች ተመድ በው እንዲሠሩ ተደርጓል ።

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ለ፪ኛ ጊዜ ጳጳሳትን ቀብተው የሾሙት በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ነው በዚህ ጊዜ የተሾሙትም ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ ፣ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስና ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሲሆኑ የእነዚህን ጳ ጳሳት ሹመት ሰበብ አድርጐ በመንግሥት አምባ ገነኑ የደርግ መንግሥት በማይመለከተው የቤተ ክርስ ቲያን ጉዳይ ገብቶ ቅዱስነታቸውን ከቀኖና ቤተ ክርስ ቲያን ውጭ ለእስራት አብቅቷቸዋል ። አዲስ የተ ሾሙትን ጳጳሳትም ያለፍትሕ እንዲታሰሩ አድርጓል።



ቅዱስነታቸው ለብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አስኬማ ጽጽበናው ሲያጠልቁላቸው



ቅዱስነታቸው ያሠሩት የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል

## ሬ. ቤተ ክርስቲያን ማሳነጽ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዛሬ የእግዚአ ብሔር ስም ዘወትር የሚመሰገንበትን ፣ ምእመናን መንፈሳዊ ግልጋሎት የሚያገኙበትን ታላቅና በጣም ዘመናዊ የሆነውን የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በጎፋ ሰፈር በግል ገንዘባቸው አሳ ንጸዋል ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ሥራው ተጠናቆ ለአ ገልግሎት ዝግጁ የሆነው ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ነው ። በዘመነ ፓትርያርክነታቸው ከፈጸሟ ቸው ዓበይት ተግባራት አንዱ የሆነው ይህ ቤተ ክርርቲያን ''ሕንፃ ወውሉድ የአብዩ ስመ'' እንደተ ባለው የቅዱስነታቸውን ስም ለትውልደ ትውልድ ሲያስጠሩ እንደሚኖር ጥርጥር የለውም ። ቅዱስነታ ቸው ቤተ ክርስቲያኑን ካሳነጹ በኋላ የተሟላ መን ፈሳዊ አገልግሎት መስጠት የሚያስችለው መተዳ ደሪያ አበጅተውለታል ።

## ማጠቃለያ፡—

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፪ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከልደት እስከ እስራት ያከናወኗቸውን ዋና ዋና ተግባሮች ባጭሩ አቅርበናል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ከ፲፱፻፴፩—፲፱፻፷፰ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲ ያን መንፈሳዊ ነፃነት በተሟላ ሁኔታ ለማረጋገጥና በትምህርት ፣ በስብከተ ወንጌል ፣ በውጭ ግንኙነት ፣ በልማትና በመሳሰሉት ዘርፎች ተልእኮዋን ለዘመኑ በሚስማማ ሁኔታ እንድትፈጽም በተወጠኑትና በተ ግባር በተተረጐሙት ሥራዎች ውስጥ ሁሉ የቅዱስነ ታቸው ዕውቀትና እጅ ያልገባበት አለ ለማለት አያ ስደፍርም ። ይህንንም ሐቅ እንኳን ወዳጆቻቸው ጠላ ቶቻቸውም አይክዱትም ።

ይሁን እንጂ ለዚች ቤተ ክርስቲያን እድገትና እርምጃ ሕይወታቸውን ሙሉ ሲሠሩ ለኖሩት ለእኒህ ታላቅ አባት ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ቆሚያለሁ ይል ከነበረው ከጊዜያዊ ጉባኤ የቀረበላቸው ገጸ በረከት ከሥልጣን ወርደው እንዲታሰሩና እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ እንዲገደሉ ለአረመኔው የደርግ መንግሥት አሳልፎ መስጠት ነው ። በዚህ ሁኔታ ሕልውናቸው እንዲያከትም የተደረጉት የቅዱስነታ ቸው ፍጻሜ መስቀሉን ተሸክመው ዕድሜያቸውን ሙሉ ሲያገለግሉት ከኖሩት ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ፍጻሜ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስለሚገኝ እጅግ የሚያሳዝን ነው ።

# የቅዱስነታቸው ሕይወት በእስር ቤት

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን የእስር ቤት ሕይወት አስመልክተን አብረዋቸው ከነበሩት መካከል በጣም ያቀርቡአቸው ለነበሩ ሰዎች ቃለ መጠይቅ አድርገንላቸው ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጥ ተውናል ፤ ሰዎችን የአነጋገርናቸው በተለያየ ቦታና ጊዜ ሲሆን ገለጻቸው ግን በጣም ተመሳሳይ ሆኖ አግኝተነዋል ፤ ይህም ስለ ቅዱስነታቸው የእስር ቤት ሕይወት የሰጡን መግለጫ ትክክለኛና እውነተኛ መ ሆኑን አረጋግጠልናል ።

ቅዱስነታቸው በመጀመሪያ ተይዘው የተወ ሰዱት ወደ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ስለ ነበረ በዚያ ስላሳለፉት አጭር የእስር ቤት ሕይወትም ከቅዱስነታቸው አንደበት የሰሙትን ሲነግሩን ፍጹ ም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የካቲት ፲ ቀን ማታ ከመኖሪያ ቤታቸው ''ትፈለጋለህ'' በማ ለት ተይዘው ወደ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ተወ ስደው ታስረዋል ፤ የታሰሩበትም ቤት የኮማንደር እስክንድር ደስታ ማረፊያ ቤት ሲሆን ፣ ብቻቸውን ነበር የታሠሩት ።

ቃለ መጠይቅ ከአደረግንላቸው ሰዎች መረዳት እንደቻልነው በታሰሩበት ቤት ውስጥ ሳሉ ከዕለታት

አንድ ቀን ፣ ከሰዓት በኋላ አንድ ኃይል መጋረጃውን ገለጥ አድርጎ ከፍ ባለድምፅ በመደጋገም "ከዚህ ምን ታደርጋለህ ? አትወጣም ወይ ? ውጣና ወደ ምሥራቅ ሂድ" ስለአላቸው ተነስተው ጋቢአቸውን በመደረብ በዘቦች መካከል አልፈው ይሄዳሉ ፤ በወቅቱ ከዘቦቹ አንዱ "ማነህ? የትነው የምትሄደው ?» ብሎ ከኋላቸው ቢጠይቃቸውም ምንም መልስ ሳይሰጡት ዘቡም ከመጠየቅ በስተቀር ምንም ሳይላቸው መሄዳቸውን ራሳቸው ቅዱስነታቸው እንደተናገሩ ቃለ መጠይቅ ያደረግንላቸው ሰዎች አውስተውናል።

ከቤተ መንግሥቱ ከወጡ በኋላ ሊሄዱ ያሰቡት ወደ አሰቦት ገዳም ነበር ። ወደ ግሪክ ኢምባሲም ለመሄድ አስበው ነበር ። ይሁንና ዋናው ሐሳባቸው ወደ አሰቦት ገዳም ለመሄድ ስለነበር በመጀመሪያ ወደ ጎፋ ገብርኤል ሄደው የአሰቦት ገዳም መንገዳቸውን ለማመቻቸት ወሰኑ ።

ወደ ጎፋ ገብርኤል የሄዱት በእግራቸው ስለነበርና መንገዱም ጠፍቷቸው ብዙ ስለተንገላቱ ከዚያ የደረሱት ከምሽቱ ፫ ሰዓት ላይ ነበር ። ይሁንና "ዘይሴሰይ እኩለየ እንስእ ሰኮናሁ ላዕሌየ" እንደተባለው አብልተው አጠጥተው ያሳደጉት ሰው ለመንግሥት ስልክ ደውሎ ሊያሲዛቸው በቅቷል ። ቀኑ ቅዳሜ ነበር ። በማግሥቱ ጧት በ፰ ሰዓት ላይ በርካታ ወታደሮች መጥተው እያሰቃዩና እየደበደቡ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት እሥር ቤት ወስደዋቸዋል ። ከዚያ ሲደርሱ ለእግራቸው ጫማ አልነበራቸውም ።

ከዚህ በኋላ ለአራት ቀናት ያህል እግራቸውንና እጃቸውን ከአልጋ ጋር ቀንም ሆነ ሌሊት ለሽንት ሲወጡ ካልሆነ በቀር በእግር ብረት ታስረው በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ሰንብተዋል ። ከአራት ቀናት በኋላ እግር ብረቱ ወልቆላቸው የቀድሞው መንግሥት ባለሥልጣኖች ታስረውበት ወደነበረው ቁጥር ፩ እሥር ቤት እንዲገቡ ተደርጓል ።

ከጎፋ ገብርኤል ተይዘው ከመጡበት ቀን ጀምሮ ለአርባ ቀናት ያህል እህል የሚባል ነገር አልቀመሱም፤ አንዳንድ ጊዜ ጣታቸውን በውሀ ውስጥ በመንከር ከንፈራቸውን ከማርጠብ በስተቀር ጥም የቆረጠ ውሀ እንኳ አልጠጡም ። አንዳንድ እስረኞች የብርቱካን ጭማቂ ይቀምሱ ነበር ብለው የሚአወሩትን በተለይ በቅርብ ይረዱአቸውና ያገለግሉአቸው የነበሩ ሰዎች ፍጹም ሐሰት እንደሆነ ይናገራሉ ። በመጀመሪያው አካባቢ ምግብ ከቤተሰብ ይመጣ የነበረ ቢሆንም አልበላም ስለአሉ ተቋርጦ ቀይቷል ብርቱካንም የሚአመጣላቸው ሰው አልነበረም ።

በተለይም በእነዚህ ከእህል በተከለከሉባቸው ቀናት ውስጥ የነበራቸው ብርታትና መንፈስ ጠንካራነት እንደተአምር የሚቆጠር እንደነበር የዐይን ምስክሮች ይናገራሉ ። በእነዚያ ቀናት ሁሉ ጸሎት ሳያቋርጡ መጽሐፍት እያነበቡና እንደምንጊዜውም ሁሉ ከሰዎች ጋር ጭውውት እያደርጉ ነበር ጊዜውን የሚያሳልፉት ። የድካም ምልክት አይታይባቸውም ነበር ።

ምግብ እንዲበሉ የደርግ ባለስልጣኖች ለምሳሌ፣ ኮ/ል ዘለቀ በየነ ፣ ኮ/ል ዳንኤልና የመሳሰሉት በተለያዩ ጊዜያት መጥተው ለምነዋቸው ነበር። እርሳቸው ግን ለመብላት ፈቃደኛ አልነበሩም ። እስከ ፋሲካ ማግሥት ድረስ ምንም ሳይቀምሱ ቆይተዋል ።

ይሁንና ፋሲካ በዋለ ማግስት ፣ ከእስረኞቹ መካከል በእድሜ ገፋ ያሉት እንደነቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ደጃዝማች ሐረጎት አባይና ሌሎችም አጥብቀውና አስጨንቀው ስለለመኑአቸው እህል ሊበሉ ችለዋል ።

በዚያን ወቅት ደርግ ለእያንዳንዱ እስረኛ ለስንቅ ብሎ ብር ፩፻፳ (መቶ ሃያ ብር) ይሰጥ ነበርና ለእርሳቸውም ቤተሰብ ብር ፩፻፳ እንዲሰጥላቸው ቢጠየቁ «አልቀበልም፣ ድሮም በልመና እንጀራ ነው የተማርኩት ፣ እየለመነ ቁራሽ የሚልክልኝ ሰው ካለ ይላክልኝ ። ያለዚያ ግን የእናንተን ገንዘብ አልፈልግም" ብለዋል ። እስከዕለተሞታቸው ድረስ ገንዘቡን ሳይቀበሉ ቀርተዋል ።

«የሚፈልጉት ምንድን ነው» ተብለው ሲጠየቁም «ከእናንተ የምፈልገው ምንም ነገር የለም ። የምፈልገው ቢኖር ገዳም ወስዳችሁ እንድታስሩኝ ነው ። ከተቻለ አሰቦት ገዳም ወስዳችሁ እሰሩኝ ፤ ካልተቻለም በፈለጋችሁት ገዳም እሰሩኝ»እያሉ አንዳንድ ጊዜ ብቅ ብለው ይጠይቁአቸው ለነበሩ የደርግ ባለሥልጣኖች ደጋግመው ነግረዋቸው ነበር፤ ይሁንና ግፈኛው ደርግ ጥያቄአቸውን አልተቀበለውም ።

ሌላው የሚአሳዝነው ሻለቃ ሴሜ የተባለለ የዘብ ኃላፊ ያደርስባቸው የነበረው ሥቃይ ነው ። ይህ ሻለቃ ምን ተልዕኮ እንደነበረው ባይታወቅም በእርሳቸው ላይ ይፈጽመው የነበረው ድርጊት ከበስተጀርባው ተልዕኮ ያለው ይመስላል ።

ከእስር ቤት እየጠራ "ስምህ አባ መልእክቱ ስለሆን አባ መልእክቱ ብለህ ፈርም ፤ በዚች አገር ወይ አንተ ወይ እኔ እንኖርባታለን ?" የሚል ዛቻ፣ ሞራል የሚነካ ንግግር ይናገራቸው ነበር ። ይሁንና ቅዱስነታቸው ባላቸው የመንፈስ ጽናት ምንም ዐይነት ፍራቻና ሽብር ሳይታይባቸው "እኔ አቡነ ቴዎፍሎስ እንጂ አባ መልዕክቱ አልይደለሁም ፤ አባ መልእክቱ ድሮ ጳጳስ ከመሆኔ በፊት እጠራበት የነበረ የዓለም ስሜ ስለሆን በምንም ዐይነት ፣ የፈለግኸውን እርምጃ ብትወስድ አባ መልእክቱ ብዬ አልፈርምም» በማለት በድፍረት ይመልሱለት ነበር ፤ ይህ ሰው የግፍ ድርጊቱን በመቀጠል ፓትርያርክ ሲሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ የሸለሙአቸውን ከወርቅ የተሠራ የእጅ መስቀል በጉልበት ቀምቶ እስረኞቹ ሁሉ እያዩት ወስዶባቸዋል ። ከሚተኙባት ትንሽ ክፍል ው

ስጥ ሰቅለውት የነበረውን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕልም ቀምቶ ወስዶታል ። ይህ ዐይነቱ በደል በእኒህ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን አባት ላይ መፈጸሙ በጣም የሚያሳዝን ነው ። ድርጊቱ የነበራቸውን እነስተኛ ነፃነት እንኳ የሚገፍ ነበር ። ቅዱስነታቸው ሕሙማንን የሚፈውሱበትን ፣ ሐዘናንን የሚአጽናኑበትን ፣ ራሳቸውንም ከጸላዩ ሠናያት የሚጠብቁበትን የእጅ መስቀል ቀምቶ መውሰዱ የዕለተ ሞቱ መጠሪያ ሆኖ ሳይሆን ይቀራልን ? እርሱም ምንም እንኳ ጊዜው በትክክል ባይታወቅም ደርግ እርምጃ ወስዶበታል ይባላል ።

ሌላው የቅዱስነታቸው የእስር ቤት ገጽታ የመንፈስ ጽናታቸውን የሚመለከት ነው ። እንደመንፈሳዊ አባትነታቸው አብዛኛው ጊዜያቸው በጾም በጸሎት የተጠመደ ነበር ፤ ድካም አያጠቃቸውም ፤ ሌሊት ሲጸልዩ ያድራሉ ፤ እስረኛው ሁሉ የሚካፈልበት ጥዋት በአንድ ሰዓት ፣ ማታ በ፲፪ ሰዓት የማኅበር ጸሎት ይካሄዳል ። ብዙውን ጊዜ ጤና ካላጡ በቀር ቅዱስነታቸው በጸሎቱ ይካፈላሉ ። አንዳንድ ጊዜም አጠር ያለ የማጽናኛ ምክር ይሰጣሉ ። እሑድ እሑድ ቅዳሴ ይካሄዳል ። በንቡረ እድ ኤርምያስ ረዳትነት ቅዳሴውን የሚመሩት ቅዱስነታቸው ነበሩ ። ፍልሰታ ከሆነች ግን ሁለቱም ሳምንት ሙሉ ምሕላ በእየቀኑ ይያዛል ። እስረኞች እንደሚሉት አንዳንድ ከፍተኛ የሆነ ፍቅረ ሃይማኖት የነበራቸው ሰዎች ሙሉ የዲቁና ትምህርት አጥንተው በጸሎት ጊዜም ሆነ በቅዳሴ ጊዜ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጉ ነበር ።

ቅዱስነታቸው ከጸሎት ውጭ አንዳንድ ከሚቀርቡአቸው ሰዎች ጋር ይጫወቱ ነበር ። ከዚህ በተረፈ ግን የቀረውን ጊዜአቸውን መጻሕፍት በማንበብ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር ሲሉ አረብኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎችን በማጥናት ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር ። የቋንቋ ጥናቱን በተለይ አረብኛ አቶ ምናሴ ያስጠኑአቸው እንደነበር ማወቅ ተችሎአል ።

ሌላው ከእስር ቤት ሕይወታቸው ልንረዳ የቻልነው ቅዱስነታቸው ትሑትና እውነተኛ መንፈሳዊ አባት መሆናቸውን ነው ። እስረኞችን ሁሉ ሰብስበው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደላችሁ ከላችሁ ይቅር በሉኝ ‘‘ብለው ይቅርታ ጠይቀው ሊኖር ይችላል ብለው የገመቱትን ቅሬታ አስወግደዋል ። ይህም ተግባር ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የሚአዝዘው ፣ ራሳቸውም በቅዱስ አባትነታቸው ምእመናንን ‘‘በዕውቀት ባለእውቀት የሠራችሁትን ኃጢአት እግዚአብሔር ይፍታ’’ ብለው የሚናዘዙት በመሆኑ ምሳሌነቱን በተግባር አሳይተዋል ።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጆች ቃለ መጠይቅ የአደረግንላቸው በእስር ቤት ውስጥ ይቀርቡአቸውና ጊዜ ሲአገኙም ያጫውቱአቸው የነበሩትን እስረኞች ስለነበር «ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ጀምሮ ቅዱስነታቸው እስከተያዙበት ጊዜ ድረስ የነበሩበትን ሁኔታ ወይም የገጠማቸውን ችግር አጫውተዋቸው እንደሆን እንዲነግሩን ጠይቀናቸው እንደሚከተለው ገልጸውልናል ።

በአንዳንድ ግለሰቦች ቀስቃሽነት ያለስማቸው ስም ለመስጠት ገና ከመነኩሴነት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ልማት በሀገርም በውጭም የአደረጉትን ጥረት ሁሉ ከንቱ ለማድረግ የተሞከረው ሙከራ ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በዘመናዊ ዕቅድ ለመምራትና ራሷን ለማስቻል ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባት የበለጠ ዘርንና አካባቢን ሳይመለከቱ የቤተ ክርስቲያን ወጣት ተማሪዎችን ወደ ውጭ አገር እየላኩ እንዳላስተማሩ ሁሉ ለአንድም ደቂቃ ያህል የሌለባቸውን ስሜት ወገንኛ አድርጎ በማቅረብ የተደረገው አሳዛኝ ሙከራ እጅግ በጣም የአሳዘናቸው መሆኑን እንደገለጹ ተናግረዋል ። በተለይም ሁሉም ሊቃነ ጳጳሳት አብረዋቸው ቢቆሙ ኖሮ የነበራቸው ዓላማ እንደዚያ እንደአልነበር ተናግረዋል ። ደርግን ለመቃወም ማለታቸው ነበር ።

ደርግም የቤተ ክርስቲያንን እርምጃ ለመቅጨጩትና እርሳቸውንም ከፓትርያርክነት ለማውረድ እንዲረዳው ጸረ ቤተ ክርስቲያን አቋም ያላቸው የእርሳቸው ተቀናቃኝ ኃይል ‘‘የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ኮሚሽን’’ በሚል አቋቁሞ የሚወስዱትን ማንኛውንም እርምጃ ይቃወም እንደ ነበረ በመራር ሐዘን ገልጸዋል ።

ደርግ ንጉሠ ነገሥቱን በገደለ ጊዜ ሁለት ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው ሄደው መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን የንጉሠ ነገሥቱን ሬሳ እንዲሰጣቸውና ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎለት በክብር እንዲቀበር ጠይቀው እንደነበር ፣ ሦስት ሰዓታት ያህል ደጅ ከአስጠናቸው በኋላ ግን አይሆንም ብሎ እንደከለከላቸው ገልጸውላቸዋል ።

ከዚህም በቀር ቅዱስነታቸው ራሳቸውንም በሚመለከት ሕይወታቸው አጭር እንደነበር በሕልማቸው ያዩአቸውን ሁለት ገሀድ ሕልሞች እንደነገሩአቸውና ደርግም የግፍ አገዳደል እንደሚገላቸው አስቀድመው ዐውቀውት እንደነበር አጫውተዋቸዋል ። ደርግም ራሱ ረጅም እድሜ እንደማይኖረው ተናግረዋል ።

የቅዱስነታቸው የእስር ቤት ሕይወት ፍጹም መንፈሳዊ ነበር ። አብዛኛውን ጊዜአቸውን በጸሎት ያሳልፉት ስለነበርና የእግዚአብሔር ጸጋ ስላልተለያቸው ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ከእስር ቤት ለግድድያ ከመወሰዳቸው አስቀድሞ የሕይወታቸው ማለፊያ እንደሚሆን ዐውቀውት ነበር ። በዚህም ምክንያት ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ስለፈለጉ ለዝግጅት የሚአስፈልገውን ሁሉ ከውጭ እንዲመጣላቸው አድ

ርገው የፋሲካ ዕለት ንቡረእድ ኤርምያስን ረዳት ቄስ አድርገው ከቀደሱ በኋላ ሥጋ ወደሙን ተቀብለዋል። ለሚጠብቃቸውም የግፍ ሞት ራሳቸውን አዘጋጅተዋል። ግድያውም አልቀረም፤ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በልዑልአሥራተ ካሣ ግቢ በአሰቃቂ ሁኔታ የግፍ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል ።

አፈጻጸሙም እንደዚህ ነው ። ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በሰባት ሰዓት ገደማ እስረኞች ሁሉ ወደመኝታ ቤታቸው እንዲገቡ ይደረጋል ። ዘበኛ ይመጣና ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅንና አቶ ሰይፉ ማኅተመሥላሴን ትፈልጋላችሁ ብሎ ወሰዳቸው ። ይገደላሉ ብሎ የአሰበ እስረኛ ግን አልነበረም ። ምንአልባት ሰው ሞቶባቸው ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት ነበር በእስረኛው ላይ ያሳደረው ፤ በነጋውም የት እንደሄዱ እስረኛው ሲጠይቅ የተሰጠው መልስ ወደ ከባድ እስር ቤት ተዛውረዋል የሚል ነበር ።

እንደገና ሐሙስ ሐምሌ ፭ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በተመሳሳይ ሰዓት ተሰብሰቡ ተባለና ፩. አቶ ዮሐንስ ኪዳነ ማርያምን ፪. አቶ አበበ ከበደን ፫. አቶ አሰፋ ድፋየን ጠርቶ አንዳንድ ብርድ ልብስና የሽንት ቤት ወረቀት ያዙ ብሎ ይዟቸው ሄደ ።

ከዚህ በኋላ እየተጠሩ የሚወሰዱት ሰዎች ሁሉ ሊገደሉ እንደሆነ እስረኛው በመላ ስለዐወቀ ከፍተኛ ፍርሃትና ሽብር ሰፈነ ። ሁሉም መሞቱ ነው በማለት ኑዛዜውን እየጻፈ አንተ ብትተርፍ ለቤተሰቤ ስጥልኝ ተባባለ ።

ዐርብ ምንም እስረኛ ሳይወሰድ ዋለ ። ቅዳሜ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በአምስት ሰዓት ገደማ እንደተለመደው ተሰብሰቡ ተባለ ፤ እስረኛ ተሰበሰበ። ዘበኛ መጣና ፩. ደጃዝማች ካሣ ወ/ ማርያምን ፪. ጀኔራል ሳሙኤልን ፫. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ስም ጠርቶ አንዳንድ ብርድ ልብስና ሽንት ቤት ወረቀት ይዛችሁ ኑ አላቸው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም ወደ ክፍላቸው ገብተው ጸሎት ከአደረጉ በኋላ በአቶ አብርሃም ወርቅነህና በአቶ አመኑ ረዳትንት ጥቁር ቀሚሳቸውን ለብሰው ነጠላ ጫማ አድርገው ቆባቸውን ደፍተው ከእንጨት የተሠራ የእጅ መስቀላቸውን ይዘው እስረኞችን ከአጽናኑና መስቀል ካሳለሙ በኋላ ‘‘እግዚአብሔር ያስፈታችሁ» በማለት ተሰናብተዋቸው ሄደዋል።

ከዚህ በኋላ ቅዱስነታቸው የት እንደደረሱ ፤ ምን ዓይነት ግድያ እንደተፈጸመባቸው ሳይታወቅ ለአስራ ሦስት ዓመታት ያህል ተደፍኖ ቆይቶአል ሆኖም «ቦጊዜ ለኵሉ» እንደተባለው ጊዜው ሲደርስ በምን አኳኋን እንደሞቱና ዐፅማቸውም የት ቦታ እንደተጣለ ማወቅ የተቻለው የሽግግሩ መንግሥት ቻርተር ባስገኘው ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ነው ።

## የቅዱስነታቸው መቃብር እንዴት ተገኘ ?

ሕይወት ተለዋዋጭ እንደመሆኗ በአንድ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ክፉና ደጋግ ዘመናት ይፈራረቃሉ ። የሩቁን ትተን የቅርቡን ታሪካችንን እንኳ ብንመለከት በኢትዮጵያ አገራችን ከ፲፱፻፷፮-፹፫ ዓ/ም የነበረው ደግ ዘመን አልፎ ክፉውና ጨለማው የደርግ ዘመን ተተክቶ ነበር ። በዚህ ዘመን በርካታ አሰቃቂ ድርጊቶች በስውርና በገሀድ ተፈፅመዋል ። በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም እጅግ ተፈላጊ የነበሩ ታላላቅ ሰዎች ፤ ጐልማሶችና ወጣቶች ያለፍትሕ ጨለማን ተገን በማድረግ እየተገደሉ ሬሳቸው እንኳ የት እንደተጣለ እንዳይታወቅ የተደረገው በእነዚህ የጨለማ ዘመናት ነው ። እንዲህ ያለ የግፍ ድርጊት ከተፈፀመባቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፪ኛ ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንዱ ነበሩ ።

አብረዋቸው ታስረው የነበሩ ፤ ነገር ግን በአጋጣሚ ከሞት የተረፉ ሰዎች እንደሚመሰክሩት ቅዱስነታቸው ለመጨረሻ ጊዜ ከታላቁ ቤተ መንግሥት እሥር ቤት የተወሰዱት ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ነበር ። ምስክሮች ሲወሰዱ ይዩ እንጂ ወዴት እንደተወሰዱና በምን አኳኋን እንደተገደሉ የትስ እንደተቀበሩ የሚያውቁት ነገር አልነበረም ። ስለዚህ የእኚህ ፓትርያርክ ሕይወት ለቤተሰቦቻቸው ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብና በመላው ዓለም ለሚገኙ ወዳጆቻቸው ፤ እንዲሁም ለሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ሁሉ ለ፲፫ ዓመታት ስውር ሆኖ ቆይቷል ። ስውር እንዲሆንም የተደረገበት ምክንያት እንኳን ለሞት ለእሥራት እንኳ የሚያበቃ ምንም ወንጀል ሳይኖርባቸው ያለፍትሕ በግፍ በመገደላቸው ነው ።

ነገር ግን ‘‘የማይታወቅ የተሠወረ የለም’’ እንደተባለው ጊዜው ሲደርስ ማናቸውም ስውር ነገር ሳይገለጥ አይቀርምና የደርግ የጨለማ ዘመን በሽግግሩ መንግሥት የዲሞክራሲ ብርሃን ሲወገድ ከንጉሡ እስከ ጳጳሱ ፤ ከወጣቱ እስከ ጎልማሳው በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደለ የትም የተጣለው ሁሉ መቃብሩ ይፈለግ ጀመር ።

ቅዱስነታቸውንም አረመኔው የደርግ መንግሥት የት እንዳደረሳቸው በይፋ መጠየቅና መቃብራቸውም መፈለግ የተጀመረው ያ የጨለማ ዘመን አልፎ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ያረጋገጠው

የሽግግር ወቅት ቻርተር ከተፈረመበት ከሐምሌ ወር ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ጀምሮ ነው ። ጥያቄው በመጀመሪያ የቀረበው በሥጋ ወንድማቸው በአቶ አበራ ጀምበሬና በአ/አበባ ጎፋ ሰፈር በሚገኘው በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ሲሆን በማከታተልም የአዲስ አበባ አድባራት ካህናትና ምዕመናን የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ፣ እንዲሁም የሌሎች ሀገረ ስብከቶች ካህናትና ምእመናን ጥያቄውን በመደገፍ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ ። በዚህ መሠረት ጥያቄው ለቅዱስ ሲኖዶስና ለመንግሥት እንዲቀርብ ተደረገ ። በዚህ ወቅት የቅዱስነታቸውን አሰቃቂ አሟሟት ያውቁ የነበሩ አቶ ቀንአ የተባሉ ሐኪም ነሐሴ ፭ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ ለጋዜጠኞች በሰጡት ቃለ ምልልስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አ/አበባ በሚገኘው በራስ አሥራት ካሣ ግቢ ውስጥ ከሌሎች እሥረኞች ጋር በሚዘገንን ሁኔታ ተገድለው እዚያው መቀበራቸውን ገለጹ ።

ስለዚህ ቤተሰቦቻቸውና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእኒህን ታላቅ አባት ሞት የተረዳው በዚች ሰዓት ነው ።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ጉዳዩን እንዲከታተሉ ለአ/አበባ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ለብፁዕ አቡነ በርናባስ ኃላፊነት ስለሰጠ ብፁዕነታቸውም ኮሚቴ አቋቁመው የመቃብሩ ቦታ ፍለጋ ተጀምሮ ወራትን ካስቆጠረ ብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ድጋፍና እገዛ አቶ ቀንአ እንዳሉት መቃብራቸው በእንጦጦ አውራጃ በከፍተኛ ፲፪ ቀበሌ ፳፪ በራስ አሥራተ ካሣ ግቢ መሆኑ ተረጋገጠ ። መቃብሩ ጥልቀት ስለ ነበረው ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ከጥዋቱ ፬ ሰዓት ቁፋሮ ተጀምሮ እስከ ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ከቀየ በኋላ ልክ ፫ ሰዓት ላይ የቅዱስነታቸው አፅም በደረት ተደፍቶ እንደተጣለ ሊገኝ ችሏል ።

## በዓይን ምስክር የተሰጠ ቃል

ቅዱስነታቸው ሲገደሉ ያየ የዓይን ምስክር አፅሙ ሲወጣ በሰጠው ቃል በራስ አሥራተ ካሣ ግቢ ውስጥ ቅዱስነታቸውንና ሌሎች ፴፫ ሰዎችን ደርግ ለግድያ ያሰለጠናቸው ኮማንዶዎች እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ በገመድ እያነቁ በየጊዜው እንደገደሏቸው ገልጿል ።

እንደ ዓይን ምስክሩ አባባል በልዩ ልዩ በታ ታሥረው የቆዩ ሰዎች ወደተጠቀሰው ግቢ ከመጡ በኋላ ወደራስ አሥራተ ካሣ መኖሪያ ቤት እንዲገቡ በማድረግ ሳያውቁ በድንገት የተደበቁት ኮማንዶዎች አንገታቸውን ሸምቀቅ ሲያደርጓቸው ወዲያውኑ ሕይወታቸው ያልፋል ።

በዚህ አሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉትን ሰዎች አስከሬኖች ሌሎች ኮማንዶዎች ተሸክመው በግቢው አጥር ሥር በምሽግ መልክ በተቆፈሩት ጉድጓዶች ውስጥ እንደሚጣል ዕቃ ወርውረው ሲሄዱ ቀባሪዎች ደግሞ በበኩላቸው ሌላ አስከሬን እስከሚደርሳቸው ድረስ አፈር ያለብሳሉ ። ሌላ ሲመጣም እንዲሁ በማድረግ በጉድጓዱ ስፋት ልክ አስከሬን ሲሞላ አፈር ይመለስበታል ። በዚህ ኢሰብአዊ ሁኔታ ነበር ግድያው የተከናወነው ።

የዓይን ምስክሩ ያን ጊዜ ይፈፀም የነበረውን የግፍ ግድያ እያስታወሱና በድርጊቱ ስቅቅ እያሉ ሲናገሩ "አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስ ተይዘው ራስ አሥራተ ቤት ከገቡ በኋላ ከላይ በተገለፀው አሰቃቂ ሁኔታ ተገድለው በተቀበሩበት ጊዜ ከእርሳቸው ጋር በዕለቱ ተገድለው ጎን ለጎን የተቀበሩት አቶ ኃይሌ ፊዳና ዶ/ር ንግሥት አዳነ ናቸው" ብለዋል ።

በወቅቱ ለብሰውት የነበረውን ልብስም የዓይን ምስክሩ ሲገልጹ "አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስ ጥቁር ነጠላ ጫማ አድርገዋል ፣ ጥቁር የሐር ቀሚስ ለብሰዋል ፣ እንደወትሮው በደረታቸው የተደረገውም ሆነ በእጃቸው የተያዘ መስቀል ግን አልነበረም" ብለዋል

ቀደም ሲል እንደተገለፀው መቃብሩ በተቆፈረበት ቀን ከአባታችን አፅም በላይ ሌላ አፅም የተገኘ ሲሆን የእርሳቸው ግን የተገኘው ጥልቀት ባለው የሥረኛው ጉድጓድ ውስጥ በደረት ተደፍቶ ነው ።

በዚህም ወቅት የለበሱት ሐር መሰል ቀሚስ ፣ ከኋላው ክፍት የሆነ ጫማቸው በራሳቸው አድርገውት የነበረው የምንኩስና ቆብ ከምን ዓይነት ጨርቅ እንደተሠራ አይታወቅም እንጂ የቆቡ ጨርቅ ተበልቶ የቆቡ ማወፈሪያ ጥጥ መሰል ነገሮች ከአፅሙ ራስ ቅል ጋር አብረው ተገኝተዋል ።

የቅዱስነታቸው አፅም የእርሳቸው መሆኑ እንዲህ በማያጠራጥር ሁኔታ ከተገኘ በኋላ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም ብፁዕን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ የመንግሥት ተወካዮች ፣ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች ከአ/አበባ አድባራት የተውጣጡ ካህናትና መዘምራን ፣ ቁጥራቸው በርካታ የሆነው ምዕመናንና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተገኙበት ከመቃብር ሲወጣና ወደ ሣጥን ሲገባ እዚያ የነበረው በሙሉ ጥልቅ ኀዘኑን በመረረ ለቅሶው በመግለጽ ዕንባ በዕንባ ተራጨ ። ከዚያም ሳጥኑ በወርቀዘቦ የተጌጠ መጎናጸፊያ ተላብሶ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ትከሻ ተይዞ የሰንበት ት/ቤት ተማሮች የፋሽስቱን ደርግ የግፍ ግድያ የቅዱስነታቸውን ታላቅ ሰውነት ፣ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ መሆናቸውን የሚጠቁም ያሬዳዊ ዜማ እያዜሙ በተዘጋጀው የአስከሬን ማጓጓዣ መኪና ውስጥ አረፈ ።

በዚህ ወቅት መቃብሩን ለመፈለግ የተቋቋመው ኮሚቴ ም/ሊሰብሳቢ የሆኑት አቶ ሰዋስው አወቀ ባደረጉት አጭር ንግግር ብፁእቡነ ቴዎፍሎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በአረመኔው የደርግ መንግሥትና በግብረ አበሮቹ አቀነባባሪነት ከሥልጣን ወርደውና ታስረው ፅኑ ሥቃይ ሲደርስባቸው ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ የት እንደደረሱ ሳይታወቅ በመቅረቱ ቤተሰቦቻቸውና ምዕመናን በከባድ ኀዘን ሲኖሩ መከራና ሥቃይ ተቀብለው በሰማዕትነት ተገድለው የሞቱበት ቦታ ተገኝቶ አፅማቸው በዛሬው ዕለት ሊወጣ የቻለው ኢህአዴግና የሽግግር መንግሥቱ ባደረጉት እርዳታ መሆኑን ገልፀዋል። አያይዘውም በተናገሩት ቃል "የእኒህ ቅዱስ አባት አፅም መገኘት ያስደሰተው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና ቤተሰቦቻቸውን ብቻ ሳይሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ስለሰብአዊ መብት የሚታገሉ ሰላም ወዳድ ድርጅቶችንና ሕዝቦችን ጭምር በመሆኑ ደስታችን ዓለም አቀፍ ይዞታ ያለው ነው ።» ብለዋል ።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስነታቸው ቤተሰቦችና በኮሚቴው ስም ለኢህ አድግና ለሽግግር መንግሥቱ ምስጋና አቅርበው ታላቁን አባት ለዚህ መከራ ካበቃቸው የአቋም መግለጫ ሞት መካከል ጥቂቶቹን በመግለጽ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ። (የተጠቀሱት የአቋም መግለጫዎች በዚሁ መጽሔት በሌላ ቦታ ላይ ተገልጸዋል)

ከዚህ በኋላ አፅሙን የያዘው መኪና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ በመንግሥት ተወካዮች ፣ በበርካታ ምዕመናንና ካህናት በቤተሰቦቻቸውና በሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በደመቀ አጀብ ታጅቦ ወደ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያን ተጉዞ አጠር ያለ ጸሎተ ፍትሐት ተደርጐለት በዚያው መቅደስ ውስጥ በክብር አርፎ እንዲቆይ ተደርጓል ።

## ቅዱስነታቸው የቤተ ክርስቲያንን መብት ለማስከበር ለወታደራዊ መንግሥት ከጻፉቸው ማስገንዘቢያዎች አንዱ

ቁጥር ፳፻፸፩/፪፻፷፯/፷፯ በተጨማሪ የቀረበ ፣
ማ ስ ታ ወ ሻ ፤
ቀን መጋቢት ፩/፲፱፻፷፯

ለኢትዮጵያ ጊዜያዊ መንግሥት
አዲስ አበባ ፣

ኢትዮጵያ በረጅም ታሪኳ ውስጥ ብዙ የችግርና የተፈተና ዘመናት ማሳለፏንና በነዚያ ዘመናትም ቤተ ክርስቲያናችን የዋናው የመከራ ገፈታ ቀማሽ ሆና እንደኖረች ሁላችሁም እንደማትዘነጉት እናምናለን ።

ብዙውን ነገር ትተን ከውጭም ሆነ ከአገር ውስጥ የተነሡ ወራሪዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ያህል ጥፋት እንዳደረሱ ለመረዳት ጉዲትና መሐመድ ግራኝ የፈጸሙትን ማስታወስና ደርቡሾች በጎንደር አካባቢ ያጠፏቸውን ድንቅ አብያተ ክርስቲያናት ፍራሾች መመልከት ይበቃል ። በሌላም በኩል ሀገሪቱ ካሏት ቋሚ የባሕል ቅርሶች የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት እርሷ ጠብቃና አሳድጋ ያቆየቻቸው ናቸው ።

እኒህና እኒህን የመሳሰሉ ብዙ ነገሮች ሁሉ ፣ ቤተ ክርስቲያኗ የፈጸመቻቸውን የረጅም ዘመናት ከፍተኛ አገልግሎት የሚያሳዩ ሲሆኑ ለመኖሪያ የሚያስፈልጋትን ድጋፍ ይነስም ይደግ የምታገኘው ከመንግሥት ነበር ። ተጋንኖ ሲነገር የኖረው ጨርሶ ያልነበራት የመንግሥታዊ ሥልጣን ድርሻና የሀገሪቱ ሲሶ መሬት ወሬ ፈጽሞ ተረት ቢሆንም ያው ያለው መጠነኛ ድጋፍ እስካሁን ድረስ ከመንግሥት ሲሰጣት ቆይቷል ።

ለወደፊትም ከመንግሥት የምትፈልገውን ድጋፍ ካላገኘችና የነበራት መጠነኛ ቋሚ ሀብትም ያለ ተመጣጣኝ ካሳ ከተወሰደባት የሚቀራት ዕድል ጨርሶ መዘጋት ሊሆን ይችላል ። በዚህ ጊዜ አንድ ሊዘነጋ የማይችል እውነት ሊነገር ይገባዋል ። በአሁኑ ጊዜ የሚባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም እንደሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ የቆየ ይዞታዋን ሁሉ አጥታ ድጋፉን ከሌሎች ትጠይቅ የሚል ይመስላል ። እስኪ ከማን ትጠይቅ ከሳውዲ አረቢያ ? ከባቲካን? ወይስ ከዓለም ሉተራን ድርጅቶች ? ይህ ሁሉ እንዳይሆንማ ጥንታዊቷና ኢትዮጵያዊቷ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን የእስልምና እምነት መሥራች የሆነው መሐመድ በዓረቢያ ከመወለዱ ከሶስት መቶ ዓመታት በፊት በገሐድ ተመሥርታ የቆየች ከዚያም ጀምሮ ንጹሕ ኢትዮጵያዊ የሆነ ትምህርትና ባሕልን ጊዜና ዓቅሟ በፈቀደላት መጠን እያስፋፋች በሀገሪቱ ላይ ከውጭ የሚሰነዘረውን ማንኛውንም የፖለቲካና የሃይማኖት ተጽእኖ በልጆችዋ አማካይነት ስትከላከል የቆየች ከኢትዮጵያ በስተቀር ሌላ ጥግ የሌላት ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት ።

ለመሆኑ በኢትዮጵያ ያለፉ የመከራ ዘመናት ሁሉ እንደርሷ ያን ያህል ቀንበር ተሸክሞ ሊታበሉ



www.ethiopianorthodox.org

የማይችሉ ታላላቅ ቅርሶች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተ የትኛው የሃይማኖት ድርጅት ነው ? የኢትዮጵያ ኦርቶክስ ቤተ ክርስቲያን በጥላቻ የሚወርድባት ስድብ ብቻ በቂ ምስክር ሆኖ ጥፋቷ ከመበየኑ በፊት እውነተኛው አቋሟና ያለፈ ክፍተኛ አገልግሎቷ ለወደፊትም ልታበረክት የምትችለው አገልግሎት ተመዛዝኖ እንዲታይላት ተቀዳሚ የስሜት ፍርድ ያልተጫነው እውነተኛ የሕሊና ፍትሕ አጥብቃ ትጠይቃለች ።

ቀደም ብለው በተገለጹትና ባልተገለጹት ብዙ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ትደገፍ ስለነበር በምዕመናን ብቻ ተደግፋ ለመኖር ምዕመናኗ የለመዱት ባሕል አይደለም ። ቤተ ክርስቲያኗ ያላትን መጠነኛ ሀብት መንግሥት ስለወረሳት ከመዘጋት መድረሳ ነው ብሎ ለምዕመናኗ እንዳይነገር ምዕመናኗና መንግሥት ተባብረው ለሀገሪቱ ጠቅላላ ዕድገትና ደኅንነት እንዲሠሩ በትምህርትና በግብር ወደፊት ለምትፈጽመው ተግባር ተቃራኒ ይሆንባታል ።

ይህ ሲሆን ትክክለኛ ፍትሕና እርዳታ መጠየቅ የሚገባት ከመንግሥት ሁኖ አግኝተነዋል ። ስለዚህ የሚከተሉት ጥያቄዎችዋ በእውነተኛ ፍትሕ እንዲሟሉላት አጥብቃ አደራ ትላለች ።

፩ኛ/ የኢትዮጵያ ገዳማት መሬት ያንድነት የማኅበር እንደመሆኑ ይኸው በይዞታቸው ያለው የንፍሮ መሬታቸው በይዞታቸው እንዲቆይ እንዲፈቀድላቸው ፣ እንዲሁም በርሷ ስም ተይዘው ሌሎች ወገኖች ሲጠቀሙባቸው የኖሩ መሬቶች ቢወሰዱ የምትጐዳበት ባይኖርም እስከዛሬ በቀጥታ ስትረዳባቸው የቆዩ አንዳንድ መሬቶች በይዞታዋ እንዲቆዩላት፦

፪ኛ/ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ካህናት ሁሉ ካህንነታቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን ስለማይሽረው እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመሬት ድርሻቸውን የማግኘት መብታቸው እንዳይዘነጋባቸው ።

፫ኛ/ ቤተ ክርስቲያን ነክ የሆኑ ዕቃዎች በሙሉ ማለት እንደ መስቀል ጽንሐ ፣ የብራና መጻሕፍት የቤተ ክርስቲያን አልባሳትና እነሱን የመሳሰሉ ከቤተ ክርስቲያኗ ሕይወት ጋር የተያያዙ ነገሮች ሁሉ ፣ የግል ሰዎች መነገጃ መሆናቸው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያኗ ድርጅቶች ቁጥጥር ሥር ሁነው ቤተ ክርስቲያኗ እንድትረዳባቸው ፣ መንግሥት አስፈላጊውን ርዳታ እንዲያደርግላት ፦



ቅዱስነታቸው ስለቤተ ክርስቲያን መብት አጠባበቅ ጉዳይ መግለጫ ሲሰጡ

፬ኛ/ ባለፈው ጊዜ ብዙ ገዳማትና አድባራት በተለያየ አቋም ይተዳደሩ ስለነበርና በአሁኑ ጊዜ የዚያ ዓይነቱ አስተዳደር መኖር ለቤተ ክርስቲያኗ ጠቅላላ አቋምና የሥራ እርምጃ ጐጂ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያኗ በአንድ የተጠቃለለ አስተዳደር እንድትደራጅ ለማድረግ የመንግሥት ድጋፍ እንዳይለያት ፦

፭ኛ/ ለሀገሪቱ ቱሪስቶችን በብዛት ከሚከቡት ጥንታውያን ቅርሶች መካከል እጅግ የሚበልጡት የቤተ ክርስቲያኗ አካሎች ስለሆኑ በነሱ ገቢም እንድትረዳ መንግሥት እንዲደግፋት ፦

፮ኛ/ ቤተ ክርስቲያናችን ፍጹም በሆነ የኅብረት ሥራቸውና አኗኗራቸው ተመሳሳይ የሌላቸው ለረጅም ዘመናት የኖሩ ገዳማት ያሏት ስለሆነች በአዲስ መልክና መንፈስ እንደነሱ የኅብረት ሥራንና የፍጹም ወንድማማችነት ኑሮን ለማሳየት ምሳሌ የሚሆኑ የካህናትም ሆነ የምዕመናን የኅብረት ሥራዎችን በተለይ የርሻና የእጅ ሥራ ማኅበሮችን በልማት ኮሚሽናችን አማካይነት ለማቋቋም ትምህርትና ስብከትም ለማስፋፋት በሚደረገው ጥረት የመንግሥት ድጋፍ እንዳይለያት ፦

፯ኛ/ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ጉዳዮች በመንግሥት አዋጅ እንዲደነገጉላትና ድንጋጌውን በሥራ ለማዋልም ከመንግሥት የምትፈልገው ሙሉ ድጋፍ እንዳይጓደልባት በቤተ ክርስቲያኗ ስም ስጠይቃችሁ የጠበቀ አደራዬን ለሕሊናችሁ ፍርድ በማቅረብ ነው ።

ማኅተም አለው
ፊርማ አባ ቴዎፍሎስ

# የቅዱስነታቸው የተቃውሞ አቋም ከደርግ

## ፖሊሲ አንጻር

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ድኅረ ኢጣልያ ወረራ ታሪክ ሲነሳ የፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ስም መነጠል አይችልም ። ይህንም ቀደም ብለን በዳበስነው የቅዱስነታቸው ሕይወት ታሪክ ውስጥ በኀላ መልኩ የተገነዘብነው ነው ። ቅዱስነታቸው ከተራ መነኰሴነት እስከ ፓትርያርክነት ዘመናቸው ድረስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ አደረጃጀትና ክርስቲያናዊ ልማት ፤ ሐዋርያዊና ዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ፤ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር መቀራረብና የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴዋ መስፋት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትን በተለያዩ አገሮች መሠራጨት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል ።

ይህን የመሰለ አስተዋፅኦና ጥረት ያደርጉ የነበሩ መላ ዕውቀታቸውንና ጉል በታቸውን ለቤተ ክርስቲያኗ ዕድገት ያለምንም ተዐቅቦ ያውሉ የነበሩ ታላቅ አባት ለምን በደርግ መንግሥት በጨለማ ታፍነው ተወስደው ሲታይ ለተመላበት አስራት ተዳረጉ ? የእነማንስ እጅ አለበት ? የሚሉትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በእያንዳንዱ ፍትህ ወዳድ ኢትዮጵያዊና ቅዱስነታቸውን በሚአውቁአቸው በውጭ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች አእምሮ ውስጥ እየተጉላሉ መሆኑ ዕውቅ ነው ።

የእነማንስ እጅ አለበት ? የሚለውን በአሁኑ ሰዓት በጥበትም ሆነ በስፋት ለመግለጽ ከአለው የጊዜ ጥበት የተነሣ የዚህ መጽሔት ዝግጅት ትኩረት ባያደርግም ወደፊት በተከታታይ የቅዱስነታቸውን የተጋድሎ ታሪክ አስመልክተው ሊወጡ በሚችሉ ጽሑፎች መገለጹ የማይቀር ነው ።

ይሁንና ከመታሰር አልፎ እስከ መገደል ድረስ ከአበቁአቸው ጽኑዕ አቋሞች መካከል እንደዋነኛ የሚታዩትን እንጠቅሳለን ።

፩ - ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ደርግ ፷፪ ባለሥልጣኖችን ያለፍርድ ከጨፈጨፈ በኋላ በሻለቃ እንዳለ ተሰማ የሚመራ የደርግ አባላት ቡድን ወደ ጠ/ቤተ ክህነት ሄዶ ስለተወሰደው እርምጃ ድጋፋቸውን ለሕዝብ እንዲገልጹ ሲጠይቃቸው ፓትርያርኩ በሰጡት መልስ «አንድ የሃይማኖት መሪ የሰው ነፍስ በከንቱ እንዳይጠፋ ይመክራል ያስተምራል እንጂ ለግፍ ተባባሪም ድጋፍ ሰጪም አይሆንም» በማለት ግድያውን አጥብቀው ተቃውመዋል ።

፪/ ግንቦት አንድ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በወጣው አዲስ ሕይወት በተሰኘው የቤተክህነት መጽሔት ገጽ ፰ ላይ እንደተገለጸው «በኢትዮጵያ የሚቋቋመው አዲስ የአስተዳደር ሥርዓት ዘለቄታ ያለው እንዲሆን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሳተፍበት እንጂ ለወታደር ብቻ የሚተው አይደለም» በማለት ወታደራዊው ደርግ በሞኖፖል ሥልጣን መያዙን እንዳልተቀበሉ በግልፅ አሳይተዋል ።

፫/ አሁንም በዚሁ መጽሔት በገጽ ፲፮ ላይ በግልጽ እንደተጸፈው «በድካምህና በላብህ ወጥተህ ወርደህ ተመገብ ፤ ሊሠራ የማይወድ አይመገብ ባለው መሠረት ሠርቶና አሠርቶ ማግኘት እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ውጭ ሌላው በደከመበት ላይ እጅን ማሳረፍ ያላስቀመጡትን ማንሣት ስለሚሆን እግዚአብሔርን ያስቆጣል» በማለት የደርግን የውርስ ፖሊሲ በግልጽ ተቃውመዋል ፤

፬/ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በቁ- ፷፻፸፩/፪፻፷፯/፷፯ ለወታደራዊው ደርግ መንግሥት በጸፉት ደብዳቤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ደርግ የወሰዳቸውንና ወደፊትም ሊወሰድ ይችላል ብላ ቤተ ክርስቲያን የገመተቻቸውን እርምጃዎች ከ፩ እስከ ሰባት በመዘርዘር ግልጽ ተቃውሞ አቅርበዋል ። (ይህን ደብዳቤ በገጽ ፳፭ ላይ ይመልከቱ ።)

፭ — የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ሞት እንደተሰማ ሁለት ሊቃነ ጳጳሳትን አስከትለው ወደ ደርግ ጽ/ቤት በመሄድ አስከሬኑ ወደ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐት ተፈጽሞለት እዚያው በተዘጋጀው መቃብር እንዲቀበር ጠይቀው ነበር ፤ ነገር ግን ጸረ ሃይማኖት የሆነው ደርግ ጥያቄውን አልቀበልም በማለቱ «እንዴት ክርስቲያን ንጉሥ ያለ ጸሎተ ፍትሐት ይቀበራሉ ? ይህ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን መጻረር ነው ።» ሲሉ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል ።

፮/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውጫዊና ውስጣዊ አገልግሎት እየሰፋ በመሄዱ ቅዱስነታቸው ጉዳዩን ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርበው ሲኖዶሱም ተጨማሪ ጳጳሳት መሾም አስፈላጊ መሆኑን ስላመነበት መስከረም — — —፲፱፻፷፰ ዓ/ም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሦስት ጳጳሳት ተመርጠው ተሾሙ ። ነገር ግን አምባገነኑ የደርግ መንግሥት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጣልቃ በመግባትና ለሃይማኖት አባቶች ምንም ክብሬታ በሌለው ድፍረት ሦስቱን ተሿሚ ጳጳሳት በተሾሙ ማግስት ሲያሰራቸው ቅዱስነታቸው ድርጊቱ የቤተ ክርስቲያንን መብት መግፈፍ ብቻ ሳይሆን ያለፍትሕ ማሰርም ሰብአዊ መብትን መጻረር መሆኑን በጽሑፍም በቃልም በመግለጻቸው ከደርግ መንግሥት ጋር በተጻራሪነት ቆመዋል ።

በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ወታደራዊው አምባገነን መንግሥት «ጊዜያዊ የተሐድሶ ጉባኤ» የተባለ አካል በማቋቋምና በዚህም ውስጥ ከአካባቢ ልዩነትና ከሥልጣን ፍላጎት የተነሣ ቅዱስነታቸውን አጥብቀው የሚጠሉ ሰዎችን በአባልነት በማሰባሰብ መሠረተ ቢስ በሆነ ውንጀላ ከሥልጣን እንዲወርዱ አድርጐና አስሮ ሲያሠቃያቸው ከቆየ በኋላ እጅግ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ገድሏቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ደም
# የሰማዕታተ ኢትዮጵያ ደም ማሕተም ነው ።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሥጋ ተገልጦ ሲሠራ ያሰበውን የቸርነት ሥራ በፈጸመ ጊዜ ለሚያምኑበት ምእመናን ይልቁንም ለመምህራኖቻቸው የሚጠብቃቸውን የተዘጋጀላቸውን የዘለዓለም ሕይወት ተስፋና በዓለም የሚያጋጥማቸውን ገልጾ ሲነግራቸው በዓለም ብዙ መከራ እንደሚጠብቃቸው ፣ እነሱ ከዓለም እንዳይደሉ ፣ እነሱን የገደለ ሁሉ ለእግዚአብሔር መስዋዕትና ቁርባን ያቀረበ እንደሚመስለው አረጋግጦላቸዋል።

ጸጋው ተስፋው መከራው ከቀዳሚ ሰማዕቱ ከቅዱስ እስጢፋኖስ ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን ተላልፎ እስከዛሬ በሥራ ላይ ፤ አለ ወደፊትም እስከዓለም ፍጻሜ ይኖራል ። እስከዛሬም ብዙ ማኅበረ ክርስቲያን በየሥራ ዘርፉ ድል ነስተው አልፈው የድል አክሊላቸውን በመቀዳጀት ፍጹም ክብራቸውን መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱባትን በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ ።

ጌታችን ሲናገር በአባቴ ቤት ብዙ ሥፍራ አለ እንዳለው እንደሥፍራው ብዛት ሀብተ ጸጋው ብዙ ተሳታፊዎቹም ብዙና ልዩ ልዩ ገድል ያላቸው ናቸው ።

በክብርም ከዋክብት በብርሃን እንደሚበላለጡና እንደሚለያዩ እነሱም ይለያያዩሉ ፣ ይበላልጣሉ ። ገድላቸው ልዩ ልዩ እንደሆነ ክብራቸውም ልዩ ልዩ ነው ።

“የፀሐይ ክብሩ ልዩ ነው ። የጨረቃም ክብሩ ልዩ ነው ። የከዋክብትም ክብራቸው ልዩ ነው ። ከአንዱ ኮከብ ያንዱ ኮከብ ክብሩ ልዩ ነው ። የሙታንም አነሳሳቸው ልዩ ነው» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቷል ።

የክርስቲያንን ሕይወት እስከዛሬ ያለበትን አካሄድ ብንመለከት እንደነብር መልክ ዝንጉርጉር ሆኖ ነው የምናገኘው ። የዚህ መሠረት የቅድስና መደብ ማኅበረ ነቢያት ፣ ማኅበረ ሐዋርያት ፣ ማኅበረ ጻድቃን ፣ ማኅበረ ሰማዕት ፣ ማኅበረ ካህናት ፣ ማኅበረ ደናግል ወመነኮሳት በመባል ተመድቦ እናገኘዋለን ። ይህ ሁሉ ግን ተጠቃሎ ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ ክርስቲያን ሲባል ማኅበረ መላእክትን ጨምሮ ደግሞ ማኅበረ በኩር ይባላል ።

“ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብ ።” የሚለው የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ መዝሙር የሚያስተባብራቸውም እነዚህ ሁሉ ናቸው።

የክርስትና ጸጋ ልደትና ተሳታፊዎች ከአሪት ከጣኦት ከሁለቱም ዓለማዊ የሕይወት ክፍል የተሰበሰቡ እንደመሆናቸው መጠን መከራውንም የተቀበሉት ከሁለቱም ክፍሎች ነው ። ከአይሁድና ከአሕዛብ ነው ማለት ነው ። እነዚህ ሐዋርያትን ተከትለው በማስተማር ሠልፍ ላይ የቆሙ ቅዱሳን ሰማዕት በፈቃዳቸው ለምስክርነት ወደ ሰማዕትነት አደባባይ ይግቡ እንጂ የመከራውን ጽዋ የጨለጡት ጋባዦቻቸው ባዘጋጁላቸው መሣሪያ ነው ።

በመስቀል ፣ በሰይፍ ፣ በእሳት ፣ በጅራፍ ፣ በማነቂያ ገመድ ፣ በጦር ፣ በመንኮራኩር ወደ አንበሳ ጉድጓድና ፣ ወደ ባሕር በመጣል ልዩ ልዩ ሥቃይና ፈተና በተሞላበት መሣሪያ ነው ።

ከኢትዮጵያ በቀር በሌላው ልዩ ልዩ የዓለም ክፍል የተነሡ ሰማዕታት ሁሉ በልዩ ልዩ መልክ የቀረበላቸውን የመከራ ጽዋ በደስታ እየተቀበሉ የጠጡ ብዙዎች ናቸው ። አጠራራቸውም ጾታ ኅሣ ያልለየ በመሆኑ ድሆችም ባለጠጎችም ታላላቆችም ታናናሾችም ተሳትፈውበታል ።

ከሐዋርያት ጀምሮ ሊቃነ ጳጳሳቱ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ፣ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣ እነ ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ ዘአንጾኪያ ፣ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሌሎችም ብዙ አበው ሰማዕትነትን ከሐዋርያዊት ሢመት ጋራ አጣምረው አከናውነዋል ። ሌሎች ነገሥታት መኳንንት መሳፍንትም ሠራዊትና የሠራዊት አዛዦች ሳይቀሩ ሥጋዊ ትጥቃቸውን በመፍታት ፣ ሥጋዊ ማዕርጋቸውን በመተው መንፈሳዊ ትጥቅ ታጥቀው ልዩ ገድል ተጋድለው የማይጠፉ አክሊላቸውን እንዳወረሱ በቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔር የፈቀደላቸውን መታሰቢያ እንዳገኙ፣ በሥጋቸው ተአምራትን በነፍሳቸውም የማይጠፋ አክሊልን እንደተቀዳጁ ቤተ ክርስቲያን መስከራላቸዋለች ፣ልዩ ልዩ መታሰቢያም አቁማላቸዋለች ።

እነ ቅዱስ እስጢፋኖስ ፣ እነ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፣ እነ ቅዱስ ፋሲለደስ ፣ እነቅዱስ ገላውዴዎስ ፣ እነ ቅዱስ መርቆሬዎስ እነ ቅዱስ ቂርቆስና ቅድስት ኢየሉጣ ፣ ቅድስት ሶፍያ ፣ የዚህ ክፍል ሠልፈኞች ናቸው ። ሌሎችም ማኅበረተኞቻቸው ከቍጥር በላይ ናቸው ።

ሁለተኛው ዘርፍ ገድሉም ጦርነቱም አፈጻጸሙም በእግዚአብሔር ረድኤት እየታገዙ ጌታችን በገዳመ ቆሮንቶስ ባሳየው ሥርዓት ባስተማረው ትምህርት የተመራ ሲሆን ቅዱሳን ጻድቃን ዓለምን ንቀው ንጽህ ጠብቀው በመኖር ከዓለም ወደ ገዳም በመሄድ የሠሩበትና ድል የነሱበት የድል አክሊላቸውንም የወረሱበት ማኅበረ ጻድቃን የተቋቋመበት የቅድስና ሕይወት ነው። ይህ መንገድ በድንግልና ሕይወት በብፅዓት እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳቸውን በመሥዋዕትነት ለእግዚአብሔር ካቀረቡ ቅዱሳን ጋራ የዓለም ጣዕም ከቀመሱ በኋላ ከዓለም ጣዕም የመንግሥተ ሰማይ ጣዕም እንደሚበልጥ ፀውቀው ዕለታዊ

መተዳደሪያቸውን ቤት ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን ቤተ መንግሥታቸውንና ዘውዳቸውን ሳይቀር ትተው ደስታቸውን ሳይጨርሱ ከሚጉላ ቤታቸው ሳይቀር ወጥተው ክርስቶስን የተከተሉ ቅዱሳን ያገለገሉበት ሥርዓት ነው ። ኋላም ምንኩስናን ጨምሮ ልዩ የድል ምልክት ይዞ ሲራመድ የኖረ የሚኖር ነው ።

እንግዲህ የዓለም ቅዱሳን ክርስቲያኖች የተጋ ድሎ መንገድ በዚህ በሁለቱ ክፍል የተመደበ ሲሆን በኢትዮጵያ የነበረው የገድል ጉዳና ሁለተኛውን መሥመር ተከትሎ የኖረ ነው ። በተጋድሎውም ቀደም ብለን እንደገለጥነው ታናሽ ፣ ታላቅ ድሃ ፣ ባለጠጋ ፣ ነገሥታትና ሕዝብ ሳይባሉ ሁሉም ተሳትፎ ያደረጉበት ነው ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ስብከትን ፣ ተባህትዎን ፣ ምንኩስናን ፣ በውስጡ የታቀፉ ልዩ ልዩ ሥርዓቶችን ያጠቃለሉ ሲሆኑ እንደነ ዓፄ ካሌብ ያሉ ፣ እንደነ ዓፄ ኢያሱ ያሉ ብዙ መናንያን ይገኙባቸዋል ።

ኢትዮጵያውያንን ራሳቸውን በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተው በሁለተኛው የገድል መሥመር ላይ ተሠልፈው ራሳቸውን ለጽድቅ በማስገዛት ልዩ ልዩ የገድል ዝግጅቶችን እራሳቸው በራሳቸው እንዲፈ ጽሙ ያደረጋቸውና ከሌላው ዓለም ልዩ አድርጎ ያሳያቸው ታላቂቱ አገራቸው ኢትጵያ ከልዑል እግ ዚአብሔር ያገኘችው ምርጫ እንደሆነ እናያለን ።

ኢትዮጵያ በሕገ ልቡና ከአበው ፣ በሕገ ኦሪት ከነቢያት ፣ በሕገ ወንጌል ከሐዋርያት ጋራ ፣ የእግ ዚአብሔር ቤተሰብ ሆና በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ እጆቿን ወደ ግፍ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር በምጽዋት በጸሎት በመሥዋዕት በአምልኮት ዘርግታ የምትኖር ስለሆነች በኢትዮጵያ ነገሥታትና ሕዝብ ውስጥ ሰውን በግፍ የሚገድሉ ሰውን ከሰው ሰውን ከአውሬ የሚያታግሉ በሃይማኖቱ ምክንያት ማንንም የሚጎዱ የሚሰቅሉ የሚገድሉ ባለመሆና ቸው የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓለም አህጉር ይልቁንም ከሮማ ፣ ከፋርስ ከባቢሎንና ከግብጽ የተለየ ሲሆን የመሪዎችና የሕዝቧም ታሪክ ከነ ኔሮን ቄሣር ፣ ከነ ዲዮቅልጥያኖስ ከነዱዲያኖስ ታሪክ የተለየ ነው ።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ራሳቸው በራሳቸው መከራ የተቀበሉ ፣ ራሳቸውን በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡ የቅዱሳን ታሪክ በስፋት ጎልቶ መታየቱ በዚህ ምክንያት ነው ።

በጉዲት ፣ በግራኝ ፣ በሱስንዮስ ዘመን ከውጪ ጠላት በተሰነዘረ ኃይል በእምነቱ የጠላት ወረራ ዘመን እንዲሁም ከለውጥ ወዲህ ማለት ከ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ወዲህ ኢትዮጵያውያን መስተጋድላን ቅዱ ሳን ከማኅበረ ጻድቃን ወደ ማኅበረ ሰማዕት እየተደ መሩ ናቸው ። በዚህ ሠልፍም ታላቁና ተጋዳዩ ሐዋ ርያ ሰማዕት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢት ዮጵያ ሰማዕታት መሪ ሆነዋል ። በገድል ለቀደሚ ቸው ለሚከተሏቸውም መሪ ናቸው ። በገድል ለቀ ደሚቸው ሆነ በገድል ለሚከተሏቸው መሪነታቸው እንዴት ነው ? ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር በዘመን የቀ ደሚቸው ኢትዮጵያውያን ሰማዕታት በማዕርግ ምን ኩስና በማዕርግ ቅስና የነበሩ ናቸው ። በሥልጣን መሢሐዊት ስለሚበልጧቸው መሪነታቸውን እንደ ማያቃውሰው መገንዘብ ይኖርብናል ።

መስተጋድላን ጳጳሳት እነ አቡነ ጴጥሮስ እነ አቡነ ሚካኤልም መኖራቸውን እንዘነጋም ። ግን ገድልና ማዕርግ አያስስተባብራቸውም።እነአቡነ ጴጥ ሮስ እና አቡነ ሚካኤል የተጋደሉ በማዕርግ ጵጵስና ሲሆን አክሊላቸውንም የተቀዳጁ በውጪ ጠላት ኃይል ነው ፤ ስማቸውም ብፁዕ ነው ።


ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ግን ገድላቸውን የፈጸ ሙት በማዕርገ ፓትርያርክነት ብፁዕ ወቅዱስ ተብ ለው ሲሆን አክሊላቸውንም የተቀዳጁት በባዕዳን ኃይል ሳይሆን በወገን ዕብሪትና ግፊት ነው ። የተፍ ጻሜ ሰማዕት ጴጥሮስ ደም ለሰማዕታተ አንጾኪያ ደም ማኅተም እንደሆነ ሁሉ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ደምም በብዙ ሺህ ለሚቈጠሩ ለሰ ማዕታተ ኢትዮጵያ ደም ማኅተም ነው ።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ሞት ታሪ ኩን እንግዳ የሚያደርገው ሳይበድሉ መበደላቸው ፣ ሳይገሉ መገደላቸው ብቻ አይደለም ። ሥጋዊውም መንፈሳዊውም ክፍል ክንዱን ያስተባበረባቸው መሆ ኑም ነው ። ለዚህም በተያዙበት ቀን "ሲጠበቅ የኖረ ፍርድ" በሚል ርእስ በጽሑፍ የወጣውን በራ ዲዮና በቴሌቪዥን የተላለፈውን መግለጫ ማስታ ወስ ይበቃል ።

በቅዱሱ የሞት ፍርድ ላይ ለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ቆሟል ተብሎ የሚነገርለት ጊዜያዊ ጉባኤና የደርግ መንግሥት ተባባሪዎች ሲሆኑ ለቤተ ክርስቲ ያን ማዕርግ ሊከላከል የሚገባው ከፍተኛው ክፍልም ከደሙ ንጹህ ሆኖ አልተገኘም ። ይህ ነው ታሪኩን ልዩ የሚያደርገው ።

ጠላቶቻቸው እንደሚሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮ ጵያ ከመንበራቸው አልወረዱም ። ከመንበር ወደ መንበር አረጉ እንጂ። በሞታቸው በደማቸውም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ልዕልና ያዕቆብ እንዳያት ሰዋሰው የብርሃን መሰላል አድርገውታል።

አንድ ትዝታ ላስታውስ እወዳለሁ ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በኢትዮጵያ ተመርጠው የመጨረሻውን ከፍተኛ ማዕርግ ቤተ ክርስቲያን ለመቀበል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተፈጸመው ሥርዓተ ሢመት ቀዳማዊ በመሆናቸውና የኢትዮጵያ ቤ/ክ እንደ እናት አብያተ ክርስቲያናት የብኵርና ባለቤት በመሆኗ ደስታ የተሰማቸው ምእመናን ፓት ያርካዊ መንበረ ወርቅ አሠርተው ሲያበረክቷቸው "መንበረ እግዚአብሔር ወበግዑ" የሚል ቃል ጽፈው ውበት ነበረ ። ይህም ቃል እንደትንቢት ሆኖ በቅዱ



ለቅዱስነታቸው በምዕመናን የተበረከተ መንበረ ክብር

ስነታቸው የሰማዕትነት ሞት ሲደመደም በቅዱስነ ታቸው የሰማዕትነት ደም ሲታተም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ "ትንብሩ ዲበ እሠርቱ ወክልዔቱ መናብርት" ካላቸው ጋራ አስራ ሦስተኛ ሆና እንድትቈጠር ሲያደርጋት ቅዱስ ሰማ ዕቱንም ማለት ሰማዕቱን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎ ፍሎስንም ወራሲ መንበር አድርጓቸዋል ማለት ይቻ ላል ። ለዚህም ምስክሩ ባልታሰበ ዕለት ባልተጠ ረጠረ ሰዓት ተገድለው ተሰውረው ከኖሩ በኋላ ባልታሰበ ዕለት ባልተጠረጠረ ሰዓት ደግሞ በስውር ከተቀበሩበት ቦታ ወጥተው ለክብር ሥፍራ መብ ቃታቸው ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንደተቀበሩ ሳይገኙ ቢቀሩም ኖሮ ሁኔታው የክርስቲያንን ልብ ሲያስጨንቅ ይኖራል ማለት ነው እንጂ ክብራቸውን ይቀንሰው ነበር ማለት አይደለም ። እንኳን የቅዱሳን ዐፅም በተፈጥሮ ውድነት አላቸው የሚባሉት ማዕ ድናትም ቢሆኑ ተቀብረው በመኖራቸው ምክንያት ኀብራቸው አይደበዝዝም፣ክብራቸውም አይቀንስም። ብዙ ቅዱሳን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ብዙ ዘመን ከኖሩ በኋላ በአንዳንድ ምልክቶች እየተገኙ አፅማቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቷል ። ታላቁ አባታችን ጻድቁ አቡነ ተ/ሃይማኖት ዐፅማቸው ከዋሻ ወደ ቤተ ክርስ ቲያን የገባው በሞቱ በ፶፰ ዓመት ነው ።

ስለዚህም ረጅም ጊዜ የመቆየቱ ነገር ዐፅማ ቸው በዚያ ቦታ መቆየቱ ቦታውን ይቀድሳል እንጂ የቅዱስነታቸው ክብር አይቀንስም "መንክር እግ ዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ። እግዚአብሔር በቅዱ ሳኑ ላይ በሚሠራው ሥራ አስደናቂ ነው" ይላል ነቢዩ ዳዊት ።

በዚህ መንሻነት ገድለ ቅዱሳን የተባለውን መጽሐፍ ስንመለከት ልዩ ልዩ ድንቅ ሥራዎች ተመ ዝግበው እናገኛለን ። ፍልሰተ ዐፅምን ፣ ርክበተ አዕፅምትን በሚመለከት ማለቴ ነው ። ነቢዩ ኤል ሳዕ እና ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ዘመን አያገናኛቸ ውም ፤ ነቢዩ ኤልሳዕ ከቅዱስ ዮሐንስ ስድስት መቶ ዓመት በፊት የነበረ ነው ። በዘመኑ ተልእኮውን ፈጽሞ ያረፈ ነው ። ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ደግሞ በዘመነ ሄሮድስ የነበረ በሰማዕትነት የሞተ ነው ። ፊተኛውና ኋለኛው ሳይተዋወቁ በዘመን ሳይገናኙ ኋላ የተነሡ ሰዎች ዐፅማቸውን በአንድ መቃብር አኑ ረውት ነበር ።

በኋላም ደግሞ በ፬፻ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ኡልያኖስ ቄሣር የዳንኤልን ትንቢት የጌታን ትምህርት ተላልፎ በቅዱሳኑ መቃብር ላይ የአይ ሁድን ምኩራብ ሊሠራ ጀመረ ። ምኩራቡ እየፈረሰ አስቸገረ። ምክንያቱን ሲጠይቅ በዚህ ቦታ የጥንት ክርስቲያኖች ተቀብረውበታልና አውጥተህ ካል ጣልክ አይጸናልህም ስላሉት ዐፅማቸውን አውጥተው እንዲያቃጥሉት ለሠራተኞች ትእዛዝ ሰጠ ። ወታ ደሮች ዐፅሙን አውጥተው ከማቃጠላቸው በፊት ምእመናን ገንዘብ ከፍለው ከወታደሮቹ ተቀብለው ወደ ግብጽ አሸሹት።በጊዜው የነበረው ቅዱስ አትና ቴዎስም በስማቸው ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ዐፅማቸው በውስጡ እንዲያርፍ አድርጓል ።

ታላቁ የክርስቲያን ንጉሠ ነገሥት ተብሎ የሚ ጠራው ቈስጠንጢኖስም ከሐዋርያት ከሰማዕታት የብዙዎችን አዕፅምት ሰብስቦ በቊስጥንጥንያ ከተማ ባሰራት አግያ ሶፊያ በተባለችው ቤተ ክርስቲያን ማሳ ረፉ በታሪክ ይነገራል ። ይህን የምናስታውሰው "ብዙኅ ሕማሞሙ ለጻድቃን ወእምኵሉ ያድኅኖሙ እግዚአብሔር ፤ እግዚአብሔር የአቅብ ኵሉ አዕፅም ቲሆሙ ወኢይትቀጥቀጥ አሀዱ እምውስቴቶሙ የፃ ድቃን መከራቸው ብዙ ነው ። እግዚአብሔር ከሁ ሉም ያድናቸዋል ። እግዚአብሔር ዐፅማቸውን ይጠ ብቃል ፤ ከዐፅማቸው አንድ እንኳ አይጠፋም ።" ተብሎ ተነግሯልና ያረፉበትን ሰዓት ምን ጊዜም ይሁን እሱ በፈቀደ ሰዓት ዐፅማቸውን ከወደቀበት አንሥቶ በክብር ቦታ የሚያሳርፈውን ሰው ያዘ ጋጃል ።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ታሪክም ይህን የመሰለ ነው ። በተገደሉ በ፲፫ ዓመት የተጣሉ በት ሥፍራ ጠፍቶ ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር በፈ ቀደው ዘመን አመፀኛው የደርግ ኃይል ወድቆ የሽ ግግር መንግሥት ተቋቁሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ ዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስና ምእመናን ጥያቄ በሽግግሩ መንግሥት በጎ ተራዳኢነት ዐፅ



www.ethiopianorthodox.org

ማቸው ከወደቀበት ተነሥቶ በዛሬው ቀን ሐምሌ ፩/፲፱፻፹፩ ዓ/ም በእግዚአብሔር ፈቃድ በክብር ቦታው እንዲያርፍ ሆኗል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ልዩነት አለው ። ለሌሎች ቅዱሳን ዐፅም የክብር ማረፊያ ቦታ ያዘጋጁ ሌሎች ቅዱሳን ሰዎች ሲሆኑ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዐፅም ግን ራሳቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለልዑል እግዚአብሔር ስም ክብር ለምእመናን አገልግሎት በገንዘባቸው በጉልበታቸው በዕውቀታቸው በሠሩት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ። ለሥራው መፋጠን ከነበራቸው ጉጉት የተነሣ በዕረፍት ጊዜአቸው የሥራ ልብስ ለብሰው ድንጋይና አፈር ሲያቀርቡ እንደነበረ ያዩ ይመሰክሩላቸዋል ። በገንዘብ በኩልም የማንንም ርዳታ ሳይጨምሩ በራሳቸው ገንዘብ ብቻ የሠሩት ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ ሕማም ሲያጋጥማቸው እንኳ ለመታከም ከማውጣት ይልቅ የሚታገሱበት ጊዜ እንደነበረ የተረጋገጠ ነው ።

እኔ ራሴም እንኳ የማውቀው ነገር አለ ። አንድ ቀን ሲያነጋግሩኝ በህማም እየተሰቃዩ ስለነበረ ‘‘ለምን ወደ ሀኪም ዘንድ ሄደው አይረዱም ? ‘‘ብላቸው’ የዚህ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ሳያልቅ ለእኔ ሕወት መጠበቂያ የማወጣው ገንዘብ አይኖርም’’ በማለት የመለሱልኝ ትዝ ይለኛል ።

ቅዱስነታቸው ምእመናን ሊገለገሉበት ለኢትዮጵያ መጠበቂያ ጸሎት ፣ ምጽዋት ፣ መሥዋዕት ሊቀርብበት እግዚአብሔር ሊመሰገንበት ለቅዱሳኑ በተፈቀደላቸው የእግዚአብሔር ፀጋ መሠረት በነቢዩ ኤልያስና በሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ስም ይህን የመካነ ሕይዋን ቤተ ክርስቲያን ሠሩ ።

ዛሬ ደግሞ ደሀርትን ከቀደምት ማስተካከል ቀደምትን ከደሀርት ማስተባበር የሚቻለው እምላክ ስማቸውን ከቅዱሳኑ ስም ጋራ አንድ አድርጐ መታሰቢያቸውንም ከመታሰቢያቸው አዋሕዶ እጽማቸው በሰሩት ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ስማቸው በሰሩት ቤተ ክርስቲያን እንዲጠራ አደረገ ።

እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን፦

ሀ/ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ፣

ለ/ የነቢየ ልዑል ቅዱስ ኤልያስ

ሐ/ የኢትዮጵያዊው ሰማዕት ወሐዋርያ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎፍሎስ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ነው ።

ስለዚህ የፍልሰተ ዐጽማቸውን በዓል በምናከብርበት በዛሬው ቀን ለመላእክት ፣ ለነቢያት ፤ ለሐዋርያት ፣ ለቅዱሳን ፓትርያርኮችና ለብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳት ለሁሉ የሚበቃ ፀጋውን የሰጠ ኢትዮጵያ ዘወትር እጆቿን የምትዘረጋለት ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ።

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን ።

አለቃ አያሌው ታምሩ

የኢት - ኦር - ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ

# ቅዱስነታቸውን ለእስራትና ለግድያ ያበቃው ውንጀላ እውነተኛ ነበር ወይ ?

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከታሰሩ ፲፫ ከተገደሉ ደግሞ ፲ር ዓመት ሆኗል ። የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ካለፉት ፲ሩት ዓመታት በኋላ ዛሬ ዐፅማቸውን በክብር ስናሳርፍ ለእስራትና ለግድያ ያበቃቸው ወንጀል እውነተኛ ነበር ወይ? የሚለው ጥያቄ በአእምሮአችን መመላለሱ አይቀርም ። ስለ ሆነም ለጥያቄው መልስ ለመስጠት የቀረበባቸውን ወንጀል ዋና ዋና ነጥብ ከቅዱስነታቸው የሕይወት ታሪክ ጋር እያገናዘብን ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል ።

በእርግጥ ለጥያቄው መልስ መስጠት የሚገባው እንደታሰሩና ከመገደላቸው በፊት ነበር ። ነገር ግን በዚያ በአፈናና በጨለማ የደርግ ዘመን መልስ መስጠት ቀርቶ ትንፍሽ ማለት እንኳ አይቻልም ነበር ። እንኳን የቀረበባቸውን ወንጀል ማስተባበል በእርሳቸው ላይ የሐሰትና የተንኮል ገመድ ሲተበተብ «ጊዜያዊ ጉባኤ» እየተባለ ይጠራ ከነበረው ስብሰባ ላይ በሐሳብ እንኳ የተለዩ ሰዎች እየተያዙ ታስረዋል ። የጥ ይት ኢላማ የሆኑም አልጠፉም ።

ዛሬ ግን ለሽግግር መንግሥቱ ምስጋና ይግባውና በተገኘው የጽሑፍ ነጻነት ያለምንም መሸማቀቅ ትክክለኛውን ማስተባበያ ለመስጠት እንሞክራለን ። ማስተባበያው ግን አጭርና ጠቃሚ እንጂ ዝርዝር ሊሆን አይችልም ምክንያቱ የአሁኑ ዝግጅት የአጭር ጊዜ እንደመሆኑ በዚህ አነስተኛ መጽሔት ሁሉንም ማካተት ባለመቻሉ ነው ። ዝርዝሩንና ረጅሙን ታሪክ ጊዜ ያወጣዋል የሚል የጸና እምነት አለን ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በተያዙ ማግሥት «ሲጠበቅ የቆየው ፍርድ» በሚል ርዕስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣው የውሸት ሐተታ እንደሚያስረዳው በቅዱስነታቸው ላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና የወንጀል ነጥቦች አምስት ናቸው ። እነዚህንም ከቅዱስነታቸው ሕያው ታሪክ ጋር እያገናዘብንና እንደሚከተለው እየገመገምን ፍርዱን ለአንባቢ እንተዋለን

፩/ የመጀመሪያው የውንጀላ ነጥብ ቅዱስነታቸው ለፓትርያርክነት የበቁት የንጉሡ ወዳጅ ስለነበሩ በጥቂት መራጮች ድምጽ ብቻ ነውና ከሥልጣን መውረድ አለባቸው ይላል ። በመሠረቱ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም የወጣው «ሐዲስ ሕይወት» የተሰኘው መጽሔት እንደሚያስረዳው ምርጫው የተከናወነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው የምርጫ ደንብ መሠረት ነው ። የምርጫው ሂደት የተመራው ፫ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፤ የወቅቱ የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅና ከምእመናን ወገን ደግሞ ፫ ስሙጥር ሰዎችን በአጠቃላይ ፯ ሰዎችን ባካተተ አስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት ሲሆን ከቅዱስነታቸው ጋር በእጩነት የቀረቡ የ፫ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ስም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን መንበር ላይ ተቀምጦ ለ፫ ቀናት ጸሎተ ቅዳሴ ከተደረገ በኋላ ነበር ። ምርጫው በተካሄደበት በመጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ከተሰጠው ድምፅ ውስጥ ቅዱስነታቸው ከመቶ ፹፤ (፹%)ድምፅ አግኝተው ነው የተመረጡት ። በጊዜው በሥራ ላይ በነበረው ሕገ መንግሥት መሠረት ንጉሡ ነገሥቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ ይባሉ ስለነበረ ይህ ምርጫ በእርሳቸው ከጸደቀ በኋላ ለሕዝብ ይፋ ሆኗል ። እንደ እውነቱ ከሆነ የቅዱስነታቸው ምርጫና አፈጻጸሙ ከእርሳቸው በፊት ከነበሩት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አመራረጥ ሰፋ ያለና ዲሞክራሲያዊ ገጽታው የጎላ እንጂ ያነሰ አይደለም ። ይህንንም ሐቅ ለማወቅ የፈለገ ተመራማሪ የሁለቱን ፓትርያርኮች የአመራረጥ ሥርዓትና አፈጻጸም ማነጻጸር ይችላል ። በተመራጮቹ ስም ላይ ፫ ቀን ጸሎተ ቅዳሴ ተደርጎበት በእግዚአብሔር አምላክ ቅዱስ ፈቃድ የተፈጸመ እንጂ ጊዜ ያዊ ጉባኤም ይሁን ደርግ እን ዳለው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ በንጉሡ ፍላጉት ብቻ የተፈጸመ አይደለም ። ደርግስ ጸረ ሃይማኖት ስለሆነ ስለ ጸሎትና ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚያውቀው ነገር የለም ። የጊዜያዊ ጉባኤ አባላትስ ? በደርግ በመኾማቸው ጸረ ሃይማኖት መንፈሱ አድሮባቸው ይሆን? የምርጫውን ትክክለኛነትና መንፈሳዊ ይዘት የተጠራጠሩት ?

ከታሪካቸው እንደምንገነዘበው ቅዱስነታቸው ለፓትርያርክነት የበቁት በችሎታቸው በሐዋርያዊ ተልእኳቸው በሥነምግባራቸው በቀና ሃይማኖታቸውና በረጅም ጊዜ ልምዳቸው መሆኑን እንኳን ወዳጆቻቸው ጠላቶቻቸውም አይክዱትም ። በአንድ ወቅት ከጊዜያዊ ጉባኤ አባላት አንዱ «ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ በትምህርትም ሆነ በእንደበተ ርቱዕነት እስካሁን ከነበሩት አባቶች በመጀመሪያው ረድፍ የሚቀመጡ ታላቅ አባት መሆናቸውን በንግግራቸው በአስተሳሰባቸው ረቂቅ ሰው እንደነበሩ በቅርብ ለማያውቃቸው ሁሉ የማስረዳ ነኝ» (አዲስ ዘመን 7/1/84 ቁጥር 117)ሲሉ የተናገሩት ትዝ ይለናል ። ስለ ቅዱስነታቸው ብቃት ነጻ አስተያየት ከሰጡ ሰዎች መካከልም ብላታ ወ/ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስ «ዝኒ ኮነ በፈቃደ እግዚአብሔር» በሚል ርእስ ባቀረቡት ጽሑፍ ያሰፈሩትን እንመልከት ።

«- - - ሰብአዊ ሕይወታቸውን በድንግልና ወስነው ለመኖር ፤ ለዲቁና ፤ ለቅስና ለምንኩስና ለቁምስና ለጵጵስና ለሊቀ ጵጵስና በቅተው፤ ባካሄድ ባነጋገር በትምህርት አሰጣጥና በስብከት አመራር ፥ ባመለካከት አንድ ታላቅ የብዙ ምእመናን አባት ሊያደርገው የሚገባውን አጥብቆ በመከታተል - - - በተጠናቀቀ ምግባርና በቀና ሃይማኖት በመወሰን መጻሕፍተ ሐዲሳትንና ፍትሐ ነገሥትን - - - በማወቃቸው ፥ ለመንግሥት ከልብ የሚያስቡና በቤተ ክርስቲያንም በኩል ብቁ ሆነው በመገኘታቸው ለዚህ ምርጫ አበቃቸው ። » (ሐዲስ ሕይወት ግንቦት ፩/፲፱፻፷፫ ገጽ ፳፫ ። )

እንግዲህ ቅዱስነታቸው ለሢመተ ፕትርክና የበቁት በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፈቃድ ፥ ሁለተኛም ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት ፥ ፫ኛም በችሎታቸው መሆኑን ከዚህ በላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች አንባቢ የሚረዳ ስለሆነ በሐሰት የወነጀላቸው ጊዜያዊ ጉባኤ ሊያፍርና ሊጸጸት ይገባዋል ።

፪/ ሁለተኛው ወንጀል « - - - ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጭ በካፒታሊስት መንፈስ በመነግግት ሕንጻ እያሠሩ በሚሊዮን የሚቈጠር ሀብት አካብተዋል - - - » የሚል ነው ። የወቅቱ የኢኮኖሚ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት የሚያገኙትን ገቢ ቆጥቦ ፥ በተቀጠበው ገንዘብ ሕንጻም ሆነ ሌላ ሥራ ሠርቶ ቋሚ ገቢ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ማስፋፋት የሚያስመሰግን እንጂ የሚያስወግዝ አይደለም ። እንደሚታወሰው ከከተማ ቦታና ቤት ዐዋጅ በፊት በአ/አበባ ከተማ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትና በራሱ በቤተ ክህነት ስም የታነጹ ፤ እንዳንድ መሳፍንትና መኳንንት ለአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ያወረሷቸው ብዙ ሕንጻዎች ነበሩ ። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ለበርካታ ዓመታት ካህናት አበል የሚያገኙት ፥ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚካሄደው ከእነዚህ ሕንጻዎች በሚገኝ የኪራይ ገቢ ነበር ። ዛሬም ቢሆን መንግሥት ከሚሰበስበው የኪራይ ገቢ ሕንጻ ለነበራቸው አብያተ ክርስቲያናት አበል መክፈሉን አላቋረጠም ።

ቅዱስነታቸውም በንዛዜ ቃላቸው እንደገለጹት ሕንጻ ያሠሩት ከባንክ ተበድረው ሲሆን ዓላማቸውም በሚገኘው የኪራይ ገቢ ቤተ ክርስቲያን ለማሳነጽና ለማስጠገን ፥ ትምህርትና ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋት ፥ እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ ካህናት መተዳደሪያ ለማበጀት እንጂ ለራሳቸው ጥቅም አይደለም ። የሚከተለውን ቃለ ኑዛዜ በጥሞና እንመልከት ።



www.ethiopianorthodox.org

«በአዲስ አበባ ከተማ በብሔራዊ ስታዲዮም በስተጀርባ የሚገኘውን በቍጥር - - - - - - - - - ካርታ የተነሣውን ቦታየንና በላዩም ላይ ያሠራሁትን ፎቅ ቤት ከነመኪና ማቆሚያ ቤቱ በሥጋ ብቻ ሳይሆን በጥምቀትም ከሥላሴ ለተወለድኩበትና ከሰፈውም የመንፈሳዊ ትምህርት ገበታ በመጀመሪያ ለተሳተፍኩበት ፤ በኋላም ጠላይቅማዛት ውስጥ ለሚገኘው ለደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያንና የሕይወቴን ዘመን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዳውል ለመረጠኝ እምላክ መመስገኛ ፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ በአዲስ አበባ በጎፋ ሰፈር አጠገብ በግል ገንዘቤ በገዛሁት ቦታ ላይ ላቋቋምሁት ለመካነ ሕይዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ርስት አድርጌ በዚህ ጽሑፍ ሰጥቻለሁ ። የስጦታውም ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

« ፩ኛ/ ቤቱን የሠራሁት ከባንክ በወለድ ተበድሬ ስለሆነ የብድሩ ገንዘብ ከነወለዱ በሙሉ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ የኪራዩ ገቢ ለዕዳው ይከፈላል ።

« ፪ኛ/ የባንኩም ዕዳ ተከፍሎ ሲያልቅ የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ ከፍጻሜ እስኪደርስ ድረስ ቤቱ የሚያስገኘው ገቢ በሙሉ ለዚሁ ሕንጻ ማስፈጸሚያ ይሆናል ።

« ፫ኛ ዕዳው ከነወለዱ ከተከፈለና የተባለውም ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ ከፍጻሜ ከደረስ በኋላ ቤቱ የሚያስገኘው ገቢ ከሁለት ተከፍሎ እኩሌታው በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ፣ እኩሌታው ደግሞ በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስም በሚከፈት ሒሣብ በባንክ እየተቀመጠ ለሕንጻው ማደሻና መጠገኛ ፤ በሁለቱም ቤተ ክርስቲያኖች ለሚቀጠሩ ለዜማ ፤ ለቅኔ ለቅዳሴና ለመጻሕፍት ትርጓሜ መምህራን ደመወዝ እንዲሁም ሰዓታት ፤ ስብሐተ ነግሕና ማኅሌት ለሚቆሙ ቅዳሴ በመቀደስ ለሚያገለግሉ ካህናት ይሰጥ ።» (ሐዲስ ሕይወት ፤ ፭/ ፱/፷፯ ፤ ገጽ ፵፯)

ደርግና ለጥፋት ዓላማው በቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ያሰለፈው ጊዜያዊ ጉባኤ በሐተታ ዘለፋቸው እንዳሉት ቅዱስነታቸው ከሠሩት ሕንጻ በሚገኘው ገቢ አውቶብስ ፤ አውሮፕላን ወይም መርከብ ገዝተው ወይም ሱቅ ሠርተው አልነገዱበትም ። ከላይ እንደተገለጸው ለትምህርት ፤ ለስብከተ ወንጌል ፤ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ለቅዱስ እግዚአብሔር መመስገኛ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ነው ያዋሉት ። ታዲያ ይህ ካፒታሊስት ፤ ነጋዴ ያሰኛልን? ፍርዱን ለአንባቢ ።

፫ኛ ሦስተኛው ውንጀላም «፭ የተለያዩ የሒሣብ ቍጥሮች በግል ስማቸው ከመክፈታቸውም በላይ በግል አሽከሮታቸውና ወዳጆቻቸው ስም ብዙ የሒሣብ ቍጥሮችን ከፍተው - - - በአሁኑ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ - - - - ብር 4,029,350 ያንቀሳቅሳሉ » ይላል ።

በእውነቱ የውንጀላው ሁሉ ውሸት ተጠቅልሎ የሚገኘው እዚህ ላይ ነው ። ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ እንደመሆናቸው አብያተ ክርስቲያናትን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያሳንጻሉ ። ትምህርት ቤቶችን ያቋቁማሉ ፤ ስብከተ ወንጌልን ያስፋፋሉ ። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ለሚያሠሩት ቤተ ክርስቲያንና ለሚመሩት ት/ቤት የሚያስፈልገው ገንዘብ በየስሙ በባንክ ተቀምጦ አስፈላጊ ሲሆን እንዲያወጣ መብት የተሰጠው ሰው እያወጣ በሥራ ላይ ይውላል ። በዚህ መልክ የባንክ ሒሳብ የተከፈተላቸው የሁለት ቤተ ክርስቲያኖች የአንድ ት/ቤት ፣ የአንድ ሀገረ ስብከት የሒሳብ ደብተሮች ቅዱስነታቸው በታሠሩ ማግሥት ጽ/ቤታቸው ሲፈተሽ ሊገኙ ችለዋል ። እነዚህም ፩ኛ ኬንያ የሚሠራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የባንክ ደብተር ቍጥር 3000 የሆነ ፤ ፪ኛ ጎፋ ሰፈር የሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የባንክ ደብተር ቁጥር 238511 የሆነ ።

፫ኛ/ የቴዎሎጂካል እስኩል የባንክ ደብተር ቍጥር 181735 የሆነ ፤

፬ኛ/ የፓትርያርክ ንብረት አስተዳደር የባንክ ደብተር ቍጥር 16,3920 የሆነ ፤

፭ኛ/ በሐረር ሀገረ ስብከት ስም የተከፈተ የባንክ ደብተር ናቸው ። ደብተሮቹ መጋቢት ፭ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ/ም በቍጥር 1/3197/69 በተጻፈ ደብዳቤ ሥራው የሚመለከታቸው ሰው እንዲረከቧቸው ተደርጎ በሒሳብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ ። ከእነዚህ በቀር ሌላ የተገኘ የሒሳብ ደብተር የለም ። እነዚህም እንደተመለከትነው በቅዱስነታቸው የግል ስም የተከፈቱ አይደሉም ። በግል ስማቸውም ያልተመዘገበውን ሒሳብ አንቀሳቅሰው ሊጠቀሙበት አይችሉም ። እነዚህ ደብተሮች በጽ/ቤታቸው ሊገኙ የቻሉት ሥራዎችን ቅዱስነታቸው ራሳቸው በቅርብ የሚቈጣጠሩ በመሆናቸውና ወቅቱ የዘረፋ ጊዜ ስለነበረ ባለባቸው ኃላፊነት የቤተ ክርስቲያንን ሀብት ለመጠበቅ ሲሉ በጽ/ቤታቸው በማስቀመጣቸው ነው ። ታዲያ 4,029,350 ብር ከየት የመጣ ነው ? ፭ የተለያዩ የሒሳብ ቁጥሮች የተባሉትስ ከየት መጡ ? ማስረጃው ምንድን ነው ? እንደ ቅዱስነታቸው ያለ መንፈሳዊ አባት አንጡራ ገንዘቡን እንዴት የተለያየ ፭ የሒሳብ ቍጥር ከፍቶ ሊያስቀምጥ ይችላል ተብሎ ይገመታል ? በየቦታው ሥራ የከፈተ ሀብታም ነጋዴ እንኳ ፭ የተለያየ የሒሳብ ቍጥር ይኖረዋል ብሎ መገመት ያስቸግራል ።

የሒሳብ ሥራ ራሱን የቻለ ባለሙያ አለው ። አንድ ሰው የራሱ ያልሆነውን ገንዘብ አባክኗል



www.ethiopianorthodox.org

ወይም በልዩ ዘዴ ለራሱ መጠቀሚያ አከማችቷል ፤ ሊባል የሚቻለው በሒሳብ ባለሙያ ተመርምሮ ሲደርስበት ነው ። የተጠቀሰው ሒሳብ ግን እንኳን በባለሙያ በተራ የሒሳብ ሠራተኛ እንኳ ተጣርቶ የተደረሰበት አይደለም ። እንዲያው በደፈናው በሐሰት በንጹሁ አባት ላይ የተለጠፈ አድፍ እንጂ እውነትነቱ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፈ አይደለም ።

፬/ አራተኛው ወንጀላ ደግሞ «በግል ፈቃዳቸውና ሥልጣናቸው ሦስት ጳጳሳትን ሾመዋል » የሚል ሆኖ እናገኘዋለን ። በመሠረቱ ጳጳሳት የሚሾሙት ክፍት ሀገረ ስብከቶች ሲገኙና የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ተስፋፍቶ አዳዲስ ሀገረ ስብከቶች ሲመሠረቱ ነው ። ስደት በበዛበት በደርግ መንግሥት ጊዜም ጭምር በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ ኢትዮጵያውያን በበርካታ ሀገሮች ስለሚገኙ የእነዚህን ወገኖች መንፈሳዊ ፍላጎት ለማሟላት ሲባል በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በውጭ ሀገር ተቋቁመዋል ። ለእነዚህ ጳጳሳት ያስፈልጓቸዋል ። በሀገር ውስጥም በሞት በተለዩ ጳጳሳት ሀገረ ስብከቶች አዳዲስ ጳጳሳት መተካት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የሚፈቅደው ሥርዓት ነው ።

ቅዱስነታቸው ከመታሰራቸው ፰ ወር ቀደም ብሎ ፫ ጳጳሳትን የሾሙት ከዚህ ፍላጎት በመነሣት ነበር ። ነገር ግን ደርግና አሜሪካኖቹ ይህንን ሹመት ከፓትርያርክ በላይ በመሆን እኛ ያልፈቀድነው ነው በማለት ተቃወሙት ። በዚህም ምክንያት ለመንፈሳዊ ተግባር ቅንጣት ታህል ክብሬት ያልነበረው ደርግ እነዚህን ጳጳሳት በተሾሙ ማግሥት ወስዶ አሰራቸው ። መከራና ሥቃይም አሳያቸው ። የደርግ አምባገነንነት በጣም ጎልቶ የታየው በዚህ በማያገባው ሲሙት ጳጳሳት ጉዳይ ጣልቃ ሲገባ ነው ። ለመሆኑ የቤተ ክርስቲያንን ፍላጎት የሚያውቁት ደርግና አሽቃባጮቹ ወይስ ፓትርያርኩ?

ስለዚህ የሮቱን ጳጳሳት ሹመት በመቃወም ደርግ በቅዱስነታቸውና በጳጳሳት ላይ የወሰደው እርምጃ በተለይም በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች ቅዱስነታቸው እስከመገደል መድረሳቸው የደርግና የአሜሪካውያኑ ግፈኛነትና ወንጀለኛነት እንጂ ሌላ የሚያሳየው ነገር የለም ።

፭/ አምስተኛውና ማጠቃለያው ወንጀላ ደግሞ « - - - ከታሪክ ሲሸሹ የወደቁ ፤ የወንጌልን ሥራ ወደጎን ገሸሽ ያደረጉ የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራትን ያፈረሱ ፤ ቤተክርስቲያን የቅርስ ደሀ ስትሆን ዝም ብለው የሚመለከቱ ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ ሥጋ አምላክን በማቀበል ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ያፈረሱ ናቸው» ይላል ።

በጠባብ የመንደርተኝነት ስሜትና በሥልጣን ፍላጎት ዓይኑ ሕሊናው የታወረ ካልሆነ በቀር የቅዱስነታቸውን ታሪክ ያነበባና የሰማ በዚህ ወንጀላ ወንጀዩን ከመታዘብ ሌላ የሚለው ነገር አይኖርም ። ቅዱስነታቸው ከተራ መምህርነት እስከ ፓትርያርክነት ሊደርሱ የቻሉት ግዙፍ ታሪክ ሠርተው እንጂ ከታሪክ ሲሸሹ አይደለም ። ከ፲፱፻፶፰ ዓ/ም ጀምሮ የስብከተ ወንጌል ድርጅት አቋቁመው በየቤተ ክርስቲያኑ እየዞሩ በመስበክ ዛሬ ለቤተክርስቲያን አለኝታ የሆነውን የሰበካ አስተዳደር ጉባኤን መሠረቱ እንጂ ከወንጌል ሥራ አልሸሹም ። የወጣቶችን መንፈሳዊ ማኅበር በመንበረ ፓትርያርኩ መሥርተው በየሀገረ ስብከቱ ቅርንጫፉን እንዲዘረጋ አደረጉ እንጂ የወጣቶችን መንፈሳውያን ማኅበራት አላፈረሱም ። ዋና የቤተ ክርስቲያን ቅርስ የሆኑትን የብራና መጻሕፍት በማይክሮ ፊልም እንዲቀረጹ ሌሎችም ቅርሶች በቅርሳ ቅርስ መምሪያ እየተመዘገቡ የሚጠበቁበትን ዘዴና ስልት ቀየሱ እንጂ ለቅርስ ጥበቃ ደንታ ቢስ አልሆኑም ። በደቡብ አሜሪካ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያናን ተከታዮች በትምህርት በጸሎትና ቍርባን በመቀበል በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጸንተው እንዲኖሩ ከማድረግ በቀር ሥርዓት አላፈረሱም ።

ስለዚህ የቀረበባቸው ወንጀላ ሁሉ ከትውልድ አካባቢ ልዩነትና ከሥልጣን ፍላጎት የተነሣ ሆን ተብሎ በተንኰል የተሸረበ እንጂ ቅንጣት ታሕል እውነት የለውም ።

# ስለቅዱስነታቸው የተሰጡ የአክብሮትና የአድናቆት አስተያየቶች

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ለዓለም ሰላምና ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት ያሳዩትን በተግባር ላይ የተመሠረተ መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ችሎታ በተለይም ከ፲፱፻፶ዎቹ ጀምሮ በፓትርያርክነት ሥልጣን ላይ እስከ ነበሩበት ጊዜ ድረስ በኢኩሜኒካል ግንኙነቶች የነበራቸውን ጉልህ ተሳትፎ እንዲሁም ሰባዊና መንፈሳዊ ሰብእናቸውን በማድነቅና በማክበር ልዩ ልዩ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ተወካዮች ጋዜጠኞችና ዕውቅ ሰዎች ከሰጡአቸው አስተያየቶች መካከል ጥቂቶቹን በጥቅስ መልክ አስፍረናቸዋል ።

## የሃይማኖት መሪዎች ተወካዮችና ዕውቅ ሰዎች ከሰጡአቸው አስተያየቶች የተወሰዱ ጥቅሶች

« - - - እናታችን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ ከመንፈሳዊ ሹማምንቶችዋ በዋጋና በችሎታ ከሁሉ ከፍ ያሉትን ቅዱስነትዎን ርዕስና መሪ አድርጋ በመምረጧ እጅግ ደስ ብሎናል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቫስኬን የመላው አርመን ቤተ ክርስቲያን ካቶሊኮስ ሚያዝያ ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም



www.ethiopianorthodox.org

፪/ « - - - ቅዱስነትዎ - - - ለዓለም ሰላም ለአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የዓላማው ደጋፊ መሆንዎ ስለማይጠረጠር - - -

« - - - ቅዱስነትዎ ለዚህ ተግባር መመረጥ ለእኛ በክርስቶስ ወንድሞችዎ ለሆነው ሁሉ ከፍ ያለ የመንፈስ ደስታን ስለአተረፈልን ከእግዚአብሔር በተሰጥዎ የፍቅር ምርኩዝ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በቅን እንዲአገለግሉአት ዕድሜ - - - እንዲአጐናጽፍዎ አምላካችን ፈቃዱ ይሁን ። » ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጁስቲን የሩማኒያ ፓትርያርክ

፫/ « - - - ባባታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ፈቃድ ለዚህ ከፍተኛ ክብር መብቃትዎ በከፍተኛ ሥራዎና በችሎታዎ ነው ። »

አባ መቃሪዮስ የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ወኪል ።

፬/ « - - - ለመላ ኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ደስታ የሆነው ይህ ከፍተኛ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክነት በዓል ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ አካል የሆኑት የመላው ምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ደስታ ነው - - - »

በእስክንድርያ የግሪክ ፓትርያርክ ።

፭/ « - - - ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ቅዱስነትዎ የሚታወቁት በኢትዮጵያ ሀገርዎ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ነው ። ለዚህ ይህ ዛሬ የተሰጥዎ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ለቅዱስነትዎ የሚገባ ነው ።»

ሜትሮፖሊታን ኒቆዲሞስ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ

፮/ « - - - ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ! ቅዱስነትዎ ለዓለም ሰላም ጥረት ከሚአደርጉት አበው አንዱ ነዎት ፤ ባለዎት ዕውቀትና ልዩ ችሎታ - - - - - - - - - - - መልካም ታሪክ ያላትን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያንን ወደፊት ከተራመዱት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር እኩል እንደእንደሚያራምዱአት ተስፋ ጥለንብዎታል ። - - - » የቡልጋሪያ ቤተ ክርስቲያን ተጠባባቂ ፓትርያርክ

፯/ «- - - - ዛሬ በመላው ዓለም ጦርነት በበዛበት በዚህ አሰቃቂ ጊዜ በኢትዮጵያ የተገኙት አዲሱ ሙሴ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ቴዎፍሎስ እጃቸውን ከዘረጉ ሳያጥፉ ስለዓለም ሰላም እንደሚጸልዩና ኢትዮጵያውያን ምእመናንም እንደ ሚረዱአቸው እናምናለን ። »

የግሪክ ሊቀ ጳጳስ የአቡነ ኤሬኒሞስ ተወካይ

«- - - ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ ይህ ከፍተኛ የፓትርያርክነት ሹመት የሰላምና የሥራ ሹመት እንዲሚሆንልዎት እንመኛለን ። » የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርክርስቲያን ፓፓ ጳውሎስ ስድስተኛ ተወካይ ፤

## ከጋዜጦችና መጽሔቶች ፡-

« - - - በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የአገራቸው የኢትዮጵያ ጳጳሳት የሚሾሟቸው አቡነ ቴዎፍሎስ ለሁለተኛ ፓትርያርክነት ተመርጠዋል» አልህራም ጋዜጣ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፷፫

«- - - ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ - - - በብሔራዊና በኢንተርናሺናል መንፈሳዊ ጉባኤዎች ላይ በመገኘት - - - - ያቀረቡአቸው ጠቃሚ ሐሳቦች እውነተኛ የሃይማኖት መሪ የሚአሰኙአቸው ሁነው ተገኝተዋል ፤ ስለትሕትናቸው ፣ ስለተመራማሪነታቸው ፤ የሌሎችን ሃይማኖት ስላማከበራቸው ለሰው ልጆች ደኅንነት አሳቢና ተቆርቋሪ ስለመሆናቸው በሰፊው ይነገራል ፤ ብጹዕነታቸው ዓለምን ተዘዋውረው ያዩ በሥልጣኔ የሚአምኑ ፣ የጊዜውን ሁኔታ አጣርተው የተረዱና ለዓለም ሰላም አጥብቀው የሚጸልዩ የሃይማኖት አባት ናቸው ።» የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ፲፱ኛ ዓመት ቁጥር ፲፱

« - - - የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለዚህ ከፍተኛ ተግባር መመረጥ የሚአጽናናውም ለዚህ ነው ። መንፈሳዊ አባትነታቸው የሚአስፈልግ ትልቅ የእግዚአብሔርና የመንግሥት አገልጋይ ታማኝ የሆኑ ሰው በመመረጣቸው የኢትዮጵያን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ብሩህ ተስፋ ሊገልጥ የሚችል ነው ። «መነን መጽሔት ፲፱ኛ ዐመት ቁ- ፳፯ ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፷፫

« - - - ይህን ማዕረግ ብፁዕነታቸው ያገኙት ያለፈው የሥራ ጊዜያቸው ጉልህ በመሆኑ ነው ።»

« - - - ብፁዕነታቸው ለሁሉም ብድግ ብለው እንግዳ መቀበልን ይወዳሉ ። ፈገግታቸውና አነጋገራቸው ወዝ አለው፡ቀና ብለው መቀመጥን ይወዳሉ፤ ሲወያዩ በሐሳብ የሚጠመዱ ይመስላሉ፤ ገና ብዙ የሥራ እርምጃ የሚጠብቃቸው መሆኑን የተረዱ ሁነው ይታያሉ ።»

« - - - ከኢትዮጵያ ትምህርት ሌላ እንግሊዝኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ ፤ ጣሊያንኛ ችሎታ አላቸው ፤ ዐረብኛ ይቀናቸዋል ። እነዚህን ሁለት ቋንቋዎች የተማሩት ሰው በመለመን በግል ጥረት ነው ፤ ለምን እንደተማሩ ሲጠየቁ « ማወቅ ይበጃል ብዬ ነው» ብለዋል ። » አዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፫

« - - - ለዚህም ነው ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ቴዎፍሎስ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዳግማዊ ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለተጐናጸፈችው ፍጹም ነጻነት ቀዳማዊ ፓትርያርክ ሆነው የተሾሙት ፣ ይህም ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱም ሕዝብ ዳግም ልደት ተብሎ ሊታሰብ ይገባዋል ። - - » ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ ።

« - - - እ ኤ ዘ- አ- በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም አመስተርዳም ላይ በተደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ብፁዕነታቸው በመገኘት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኩል አስፈላጊውን ጥያቄ ለጉባኤው አቅርበዋል ፤ - - - የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል እንድትሆን ስለአደረጓት ብፁዕነታቸው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ባለውለታ አባት ናቸው ።

« - - - ትዕግሥት ፣ ክፉን በክፉ አለመቃወም ፤ ኅድዓት ወይም ዕርጋታና እርቆ አስተዋይነት በተፈጥሮ ጸጋ የተገኙ የብፁዕነታቸው የተለዩ ሀብታት ናቸው ። «ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ፤ ፳፭ኛ ዐመት ቁ-፷፫ ።

www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስነታቸው የሰማዕትነት ውሳኔ

**የቅዱስነታቸውን የሰማዕትነት ውሳኔ ሊያስረዱ ከሚችሉ ሐሳቦችና አስተያየቶች መካከል በሁለት አጋጣሚዎች የተናገሩአቸውን እናዘክራለን ።**

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሐሰተኞች እየተወነጀሉ ለእሥራት በተቃረቡበት ጊዜ አንዳንድ የሚያቀርቧቸው ሰዎች እንዲሸሹ መክረዋቸው ነበር። እርሳቸው ግን የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ ለመጋፈጥ ቆርጠው ስለነበረ ምክሩን አልተቀበሉትም ይልቁንም ቆርጠኛ ውሳኔአቸውን በሚከተሉት አባባል ገልጸዋል ።

"እኔ ከዚህ ደረጃ የደረስኩት ክትቢያ ተነስቼ ነው ። በሰላሙ ጊዜ ስሾም ፣ ስሸለም ፣ አባታችን ፣ አባታችን እየተባልኩ ስከበር ኖሬያለሁ ። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ ያሉት ታላላቅ ሰዎች እየታሠሩ ያለፍትሕ እየተገደሉ ነው ። እኔም እንደእነሱ በዚሁ በሀገሬና በቤተ ክርስቲያን ስም የሚደርስብኝን ማናቸውም መከራ መቀበል እንጂ መሸሽ ተግባሬ አይደለም ። አባቶቼ ሐዋርያትና ሰማዕታት ስለእውነትና ስለቀናች ሃይማኖታቸው ሲሉ በሰይፍ ተቆርጠው ፣ በገመድ ታንቀው ፣ በእሳት ተቃጥለው በሰማዕትነት ተሠውተዋል ።

«እኔም እንደ እነሱ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክብር ስል እስክሞትም ድረስ ቢሆን መከራና ሥቃዩን ከመቀበል በቀር ወደኋላ የምልበት ምክንያት የለም ። ቀደም ሲል በአኑ አቡነ ጴጥሮስ ላይ የደረሰው የሰማዕትነት ሞት እኔም ቆርጬ የእነሱን ጽዋ እንድቀበል እንጂ እንድሸሽ አይገፋፋኝም ። ለእኔ ሕይወት ስል በብዙ ድካም የተገኘውን የቤተ ክርስቲያን ክብር አላዋርድም ፤በአንገቴ ላይ ስለት እያንገዋበበ እንደሆነ ይታወቀኛል ። ቢሆንም እዚህ ሆኜ የሚመጣብኝን መከራ ለመቀበል ዝግጁ ስለሆንኩ በምንም ተአምር አልሸሽም ።»

በአንድ ወቅት ቅዱስነታቸው ለመቀየሪያ የግል ልብሳቸውን እንዲያመጣላቸው ስንቅ ለሚያቀብላቸው ሰው መልእክት ያስተላልፋሉ ። ስንቅ አቀባዩም ይህንኑ መልእክት ለጠ/ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅና ለወቅቱ ፓትርያርክ አድርሶ ልብሱ ከመንበረ ፓትርያርክ መኖሪያቸው ወጥቶ እንዲሰጠው ቢጠይቅ ፓትርያርኩ የደርግ መንግሥት ካላዘዘ አይሰጥም ብለው ይከለክሉታል። እሱም በዚህ ሁኔታ ልብሱን ማግኘት እንዳልቻለ ገልጾ ለቅዱስነታቸው መልእክት ሲያስተላልፍላቸው ጉዳዩን በሚከተለው አባባል ደምድመውታል ።

«ከዛሬ ጀምሮ ምንም ነገር ከማንም እንዳትጠይቅ «ዕፀዋትን በልዩ ልዩ ቀለማት ያስጌጠ ለጋሱና ቸሩ አምላካችን ለእኔም የምለብሰው አያሳጣኝም ። የመጨረሻውን ልብሴን እሱ አዘጋጅቶልኛል» ። ሲሉ የሚጠብቃቸውን ኅልፈተ ሕይወት ተንብየዋል ።